# ገበሬውና ፡ ሚስቱ ።



ተጻፈ ፡

ከተፈሪ ፡ ደፈረሱ ፡

(ዘደብረ ፡ ሊባኖስ) ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.

ዋጋው ፡ ፩ ፡ ብር ፡ ከ፳፭ ፡ ሳንቲም ።

# ገብሬውና ፡ ሚስቱ ።

ተጻፈ

ከተፈሪ ፡ ደፈረሱ ፡

(ዘብሔረ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ) ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.

በተስፋ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ማሳተም ፡ ክልክል ፡ ነው ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

## መ ግ ቢ ያ ።

ገበሬዎችንና ፡ የገበሬዎችን ፡ ሚስቶች ፡ አእምሮ ፡ ማጐልመሻ ፡ ኅብረትና ፡ ሥራ ፡ ይቅርና ፡ ትሕትና ፡ በአንድነት ፡ ከተዳመሩ ፡ ችግር ፡ እየሸሸ ፡ ማግኘት ፡ እየቀረበ ፡ የሚገኝ ፡ በመሆኑ ፡ «ገበሬውና ፡ ሚስቱ ፡» በማለት ፡ ሰይሜ ፡ ፩፡ መጽሐፍ ፡ ለማውጣት ፡ በማቀድ ፡ የጻፍኩትን ፡ ጽሑፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ በተቻለኝ ፡ ስሜት ፡ መጠን ፡ ይህን ፡ አንባቢዎች ፡ ወደፊት ፡ የምትመለከቱትን ፡ ሃሳብ ፡ በመፈጸሜ ፡ ምስጋናዬ ፡ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሁን ፡ እላለሁ ።

በተመለከተው ፡ አርእስት ፡ መሠረት ፡ ጉዳዩ ፡ አያሌውን ፡ ትጉሕና ፡ ጠንካራ ፡ ሴት ፡ የባሏ ፡ ሐብትና ፡ ገንዘብ ፡ ከመሆኗም ፡ በላይ ፡ ባሏን ፡ በመምከርና ፡ የባሏ ፡ ታዛዥ ፡ መሆንን ፡ በመግለጽ ፡ እንዲሁም ፡ ትንሹን ፡ ቆጥባ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ማድረግ ፡ የባለ ፡ ሙያ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ትልቁ ፡ ሙያዋና ፡ ተግባሯ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ስያሜ ፡ በእርግጠኛው ፡ በእርሻ ፡ ላይ ፡ ለሚገኙት ፡ ወንድሞቼና ፡ እኅቶቼ ፡ ለስሜታቸው ፡ ተጨማሪ ፡ የሚሆንና ፡ ድጋፍ÷አርአያ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ በስሜት ፡ አመራር ፡ የገለጽኳቸው ፡ አስተያየቶች ፡ የሚረዱ ፡ ስሜት ፡ ሆነው ፡ በፍቅር ፡ ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ እንዴት ፡ እንደሚረዳና ፡ እንደሚጠቅም ፡ ከባዱን ፡ ችግር ፡ ለማቅለል ምን ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ስገልጽ ፡ ድካሜም ፡ ለዚሁ ፡ ስሜት ፡ አገላለጽ ፡ መሆኑን ፡ ለአንባቢዎች ፡ ለመግለጽ ፡ ሐሳቤን ፡ በዚች ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜዬ ፡ በደረስኳት ፡ መጽሐፍ ፡ አስፍሬአለሁ ።

## አስተዳደር ።

አስተዳደር ፡ ማለት ፡ ከመተዳደር ፡ የሚወረስ ፡ አንድ ፡ ነፃ ፡ ሕዝብ ፡ የሥልጣኔ ፡ (ሲቭልሺን) ፡ አያያዝና ፡ አመራር ፡ ይሆናል ።

በተረፈም ፡ የመንግሥቱን ፡ አደራና ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብለው ፡ በሚያስተዳድሩበት ፡ ክፍል ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ተግባር ፡ የሚመራ ፡ ሰው ፡ ተመስጋኝና ፡ የአስተዳደርን ፡ ዘዴ ፡ የሚያውቅ ፡ ለመሆኑ ፡ የሚአውቀው ፡ በክፍል ፡ ግዛቱ ፡ የሚተዳደረው ፡ ሌላ ው ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ።

፩ኛ ፡ ተጂ ፡ በሚባለው ፡ ሀገር ፡ በምክትል ፡ ገዥነት ፡ ለሚያስተዳድሩ ፡ ባሻ ፡ በቀለ ፡ ወዥቡ ።

፪ኛ ቱሉ ፡ በሎ ፡ በተባለው ፡ ወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥብቅ ፡ ዳኛ ፡ ለሆኑት ፡ አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገብረ ፡ ወልድ ።

፫ የተጂ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊ ፡ ለሆኑት ፡ አቶ ፡ ምሕረት ፡ ባንጃው ፡ አነቃቅተው ፡ ይህቺን ፡ ገበሬውና ፡ ሚስቱ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ የተዘጋጀች ፡ መጽሐፍ ፡ እንዳሳትም ፡ ስለአሳሰቡኝ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ምስጋናዬን ፡ ከልብ ፡ አቀርባለሁ ።

በተለይም ፡ በ፩ኛ ፡ ተራ ፡ መስመር ፡ የተጻፉት ባሻ ፡ በቀለ ፡ ወዥቡን ፡ ሳላስብ ፡ ወይንም ፡ ሳላስታውስ ፡ እንዳላልፍ ፡ ሕሊናዬ ፡ ስላስገደደኝ ፡ ባላቸው ፡ መልካም ፡ አስተያየትና ፡ የማበረታታት ፡ በጐ ፡ ፈቃድ በድጋሚ ፡ ሳላመሰግናቸው ፡ አላልፍም ።

## መቅድም ።

እግዚአብሔር ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ ፈጥሮ ፡ እርሷ
ም ፡ ምግብና ፡ ፀጋ ፡ ለመሆን ፡ ከምትችለው ፡ ገነት ፡ ውስጥ
አኑሮ ፡ ክፉና ፡ ደግን ፡ የምታሳውቀውን ፡ የዕፀ ፡ በለስ ፡ ፍሬ
እንዳይበሉ ፡ እንዳዘዘና ፡ እነሱም ፡ አምላክ ፡ ለመሆን ፡ በጋ
ለ ፡ የማዕበል ፡ ፍላጐት ፡ ተነድለው ፡ በሰይጣን ፡ አሳሳችነት
ተታለው ፡ ከገነት ፡ እስከ ፡ ተለዩበት ፡ ድረስ ፡ የሰው ፡ ልጆች
በአለንበት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አጥንታቸውን ፡ ሳይሰብሩ ፡ ላባቸ
ውን ፡ ሳያንቆረቁሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፀጋ ፡ እየተመገቡ
ይኖሩ ፡ እንደነበረ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ጉልህ ፡ ማስረጃ ፡ ስለ
ሚሆኑ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የእረፍትና ፡ የድካም
ጊዜ ፡ መዘርዘር ፡ አንባቢዎችን ፡ ከማድከም ፡ ሌላ ፡ ትርፍ
የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ የቀረውን ፡ ዝርዝር ፡ ለፍጥ
ረት ፡ ተመራማሪ ፡ ሊቃውንቶች ፡ በመተው ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ጥረህ ፡ ግረህ ፡ በላብህ ፡ ትርፍ ፡ ኑር ፡ ብሎ
አምላካዊ ፡ ትእዛዙን ፡ ከሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ስላለው
በጥቂት ፡ ስናገር ፡ ጉዳዩን ፡ ለመተረክ ፡ ሳይሆን ፡ ለድርሰቱ
መግቢያ ፡ መሆኑን ፡ አንባቢ ፡ እንዲገነዘበው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ም
ኞቴና ፡ እምነቴ ፡ ነው ።

የሰው ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ በአውቶሚክ ፡ ዕድ
ሜ ፡ በእርሻ ፡ ጥበባቸው ፡ ተራቀው ፡ ተራራን ፡ በማፍረስ
ሜዳን ፡ በማረስ ፡ ውቅያኖስን ፡ ገድበ ፡ እንደ ፡ ሱዊስ ፡ ካናል
ያለውን ፡ የመርከብ ፡ መተላለፊያ ፡ በር ፡ ለመሥራት ፡ የሚ
ያስችል ፡ ጥበብና ፡ እውቀት ፡ ሳይኖራቸው ፡ ሕይወታቸውን
እንደምን ፡ ሊያስተዳድሩ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ፡ ብለን ፡ እራሳች
ንን ፡ ብንጠይቅ ፡ በጣም ፡ ወደሚአስቅና ፡ ወደሚአስደንቅ

ጉዳይ ፡ ዝርዝር ፡ እንገባለን ። ይኸውም ፡ በድንጋይ ፡ ዘመን ተብሎ ፡ የሚጠራውና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የእሳትን ፡ ጥቅም ከማወቁ ፡ በፊት ፡ አእዋፋት ፡ በጥበብ ፡ በልጠውት ፡ መታ የታቸውን ፡ ለመረዳት ፡ ያህል ፡ ብልሁ ፡ ሰው ፡ እንደሞኝ ወፍ ፡ ዘራሽ ፡ ያሆኑትን ፡ እፀዋት ፡ እየፈለገ ፡ እራሱ ፡ ለመ ዝራት ፡ ጥበብ ፡ ስላልነበረው ፡ ይህችን ፡ ወፍ ፡ ዘራሽ ፡ ፍሬ አጋምም ፡ ሆነች ፡ ቀጋ ፡ የፍጥረት ፡ ጓደኛው ፡ እንዳይነካበ ት ፡ ሹል ፡ ድንጋይ ፡ እየፈለገ ፡ ሲጠብቃት ፡ እንደነበረ ፡ ታሪ ክ ፡ ይነግረናል ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በአምላኩ ምሳሌና ፡ ባሕርይ ፡ የተፈጠረ ፡ መሆኑ ፡ የማይካድ ፡ ስለሆነ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያለ ፡ መጀመሪያ ፡ በሹል ፡ ድንጋይ ፡ በኋላ ፡ በጦር ፡ በኋላም ፡ በዶማ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሹል ፡ ብረት ፡ ሠርቶ ፡ በፍጥረት ፡ ወንድሙ ፡ እያስገመተተ ፡ ሲያርስ ፡ ኖሮ ፡ ጊዜ ሙያውን ፡ እየለወጠለት ፡ በመሄዱ ፡ በፈረስና ፡ በበሬ ፡ እያ ረሰ ፡ ሲኖር ፡ ቆይቶ ፡ መሬት ፡ ታላላቅ ፡ የሲያንስ ፡ ሊቃውን ቶች ፡ መፍጠር ፡ ከጀመረችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እነሆ ፡ በሞተር ፡ ጀምረን ፡ ድሮ ፡ በ፩፲ ፡ በሬ ፡ የሚዋልበትን ፡ መሬት ፡ ዛሬ ፡ በ፲፱ ፡ ሰዓት ፡ ማፍረስና ፡ ማረስ ፡ ቻለ ፡ ሃገራችንም ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ከ፫ሺ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ተከብራና ፡ ተፈርታ ፡ በነ ፃነቷ ፡ ታውቃ ፡ የኖረችው ፡ በሲያንስና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሌላ (ሌተራትሮች) ወይንም ፡ መልካም ፡ ጥበቦች ፡ ሳይሆን ፡ ሞፈ ርና ፡ ቀንበር ፡ በሚአቀዳጁ ፡ ጠንካራ ፡ ክንድ ፡ ባላቸው ፡ ል ጆችዋ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የሚክደው ፡ ነው ፡ ብዬ አልገምትም ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ በመኖርና ፡ ባለመኖር ፡ መከከል ፡ ያ ለው ፡ ክርክር ፡ ሲነሳ ፡ ሰው ፡ ያለምግብ ፡ ኑሬ ፡ ያለ ፡ ግድ ብ ፡ ዓይኖርም ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ አብሮ ፡ የሚሰለፍ ፡ አን ፃራዊ ፡ ቃል ፡ በመሆኑ ፡ በተለይም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከቀሩት

ያለም ፡ ክፍሎች ፡ እንድትስተካከል ፡ አስቦ ፡ የሰማዩ ፡ መስ ፍን ፡ የንጉሦች ፡ ንጉሥ ፡ የፍጥረቶች ፡ ጌታ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃ ይለ ፡ ሥላሴን ፡ ከሰጠን ፡ ጀምሮ ፡ እርሻ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ክብር እንዳገኘና ፡ ኢትዮጵያም ፡ በእርሻዋ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ምን ፡ ያ ህል ፡ ከፍ ፡ እንዳለች ፡ ስለማወቅ ፡ በገበሬነቴ ፡ ከልብ ፡ እኰ ራበታለሁ ።

## የተከበራችሁ ፡ አንባቢዎች ።

የዚህች ፡ ድርሰቴ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት፡ ሳትሆን ፡ አንድ ፡ ገበሬና ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ተደጋግፈው ፡ ከኖ ረ ፡ የችግርን ፡ ማዕበል ፡ ፈንቅለው ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ የሚ ችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚአስረዳ ፡ የዓይን ፡ ምስክር ፡ የሚ ገኝላት ፡ ስለሆነች ፡ አንባቢዎችን ፡ እንዳላደክም ፡ ዝርዝሩ ን ፡ አሳጥሬ ፡ ወደፍሬ ፡ ነገሩ ፡ በቀጥታ ፡ ገብቻለሁ ። ከላይ እንደዘረዘርኩት ፡ ሁሉ ፡ በድርሰት ፡ ደንብ (አክቱን) ማስቀ ደም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ተስኖኝ ፡ ሳይሆን ፡ የአንባቢዎች ን ፡ ጊዜ ፡ ለመቆጠብ ፡ ያልኩት ፡ ስለሆነ ፡ ይኸቺን ፡ መጽ ሐፍ ፡ ጀምሮ ፡ በማንበብ ፡ የጨረሰ ፡ አንድ ፡ በበሬ ፡ የሚአ ርስ ፡ ደሐ ፡ ገበሬ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ እንደማይሳን ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነትዋ ፡ ለዘላለም ፡ ትኑር ።

## ገበሬው ፡ ለሚስቱ ፡ በሰኔ ።

ተወዳጅዋ ፡ ሚስቴ ፡ በጣም ፡ የምወድሽ ፡
ዘወትር ፡ ከልቤ ፡ ፍጹም ፡ የማልለይሽ ።
ጣድ ፡ አድርጊውና ፡ የጐመኑን ፡ ምንቸት ፡
እኔም ፡ እመጣለሁ ፡ ለቃቅሜ ፡ እንጨት ።
እሷ ፡ ከደረሰች ፡ ለጧት ፡ ቊርሳችን ፡
ደግሞ ፡ ለማታችን ፡ ክርስቶስ ፡ አለን ።

ሚስት ፡ ለባሏ ፡ እሺ ፡ የኔ ፡ አካል ፡ ባዘዝከኝ ፡ እውላለሁ ፡
እንኳን ፡ ስትረዳኝ ፡ እኔም ፡ እጥራለሁ ።
አይዞህ ፡ የኔ ፡ አካል ፡ አትበሳጭ ፡ ብዙ ፡
እንድከም ፡ እንጣር ፡ ሳንሆን ፡ የሰው ፡ ግዙ ፡
በሰው ፡ እጅ ፡ ማደር ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ መዘዙ ።
ቡሬና ፡ ዳለችን ፡ ውጣና ፡ እያቸው ፡
ወሐም ፡ እንዳልጠጡ፡ወስደህ ፡ አጠጣቸው ፡
ጥሩ ፡ ሣር ፡ አለበት ፡ ወስደህ ፡ ጠብቃቸው ።
(መግባቸው)

ገበሬው ፡ ለሚስቱ ፡ ሰማሽ ፡ ወይ ፡ የኔ ፡ ውብ ፡ ልንገርሽ ፡ የሆዴን ፡
ለቊርስ ፡ የተጣደች ፡ የጧት ፡ ጐመናችን ፡
ልትሆን ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ ለማታ ፡ ራታችን ።
እሷን ፡ ስጠባበቅ ፡ እቤቴ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡
ፍጹም ፡ አልተሠራም ፡ እንግዲህ ፡ ሥራዬ ፡
ሆዴ ፡ ተገናኝቷል ፡ ከኋላው ፡ ጀርባዬ ።
እንዴት ፡ ተነስቼ ፡ በሮቹንስ ፡ ልዩ ፡
የረሐብን ፡ ነገር ፡ ታውቂው ፡ የለም ፡ ወዩ ።

ሚስት ፡ ለባሏ ፡ ሣላውቀው ፡ ቀርቼ ፡ አይደለም ፡ ችግሩን ፡
ማሰብ ፡ ያስፈልጋል ፡ ከዛሬ (የ) ነገውን ፡

በሙሉ ፡ አጠንፍፌ ፡ ባወጣ ፡ ሁሉን ።
ሆድ ፡ አዲስ ፡ እንግዳነው ፡ ውቅያኖስ፡ባሕር ፡
ተከብረን ፡ ስንኖር ፡ በስውር ፡ ምሥጢር ፡
እንዋረድ ፡ ብለህ ፡ ነገር ፡ አትጀምር ፡
ቻለው ፡ እንዳለፈው ፡ ስትግደረደር ።

ገበሬው ፡ ለሚስቱ ፡

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ምክር ፡ ስትመክሪኝ ፡ ውለሽ ፡
ረሐቤን ፡ ስነግርሽ ፡ ምናርግ ፡ ትያለሽ ።
ይሰማኛል ፡ ብለሽ ፡ ወሬ ፡ አታበላሺ ፡
በታኅሣሥ ፡ ይሁን ፡ ይሄ ፡ ጨዋታሽ ፡
ሂጂ ፡ ካጠገቤ ፡ ግቢ ፡ እንዳሽ ።

ይልና ፡ በረሐብ ፡ መንፈስ ፡ ተቆጥቶ ፡ ይተኛል ።

ሚስት ፡ እራት ፡ ታቀርባለች ፡

እራታችን ፡ ቀርቧል ፡ ተነስ ፡ እንመገብ ፡
ውረድ ፡ ከመደቡ ፡ እጅህንም ፡ ታጠብ ፡
ሣላውቅ ፡ አልቀረሁም፡ስለ፡አንተም፡መራብ።
እየመሰለኝ ፡ ነው ፡ ትንሽ ፡ የምንቆጥብ ።

ትለውና ፡ ይመገባሉ ፤

ገበሬው ፡ ከበላ በኋላ ፡

ስለ ፡ ቀኑ ፡ ምክርሽ ፡ አሁን ፡ ባሰበው ፡
የጧት ፡ ቍርሣችንን ፡ ወዲያው ፡ ብንበላው ፡
አስበሽ ፡ ለማታ ፡ ባትቆጥቢው ፡
ባሁኑ ፡ የራት ፡ ጊዜ ፡ የት፡ ነው፡ መድረሻው ።
እንዲህ ፡ ያለ፡ምክር ፡ እውነትም፡ ይጠቅማል ፡
ቍርሱን፡ያልበላ፡ሰው፡እራት፡እንዴት፡ያጣል ።
እንጣጣር ፡ በጣም ፡ እንግዲህ ፡ ለሥራ ፡
ሰኔም ፡ ማለቁ ፡ ነው ፡ እንደዚያ ፡ ስንፈራ ።

## ገበሬው ፡ ለሚስቱ ፡ በሐምሌ ።

የሐምሌም፡መግቢያው፡ነው፡ ዘሩም ፡ ተዳረሰ ፡
ካለፈው ፡ ሐሳቤ ፡ የአሁኑ ፡ ባሰ ።

ሚስት ፡ እያደርክ ፡ እወቀው ፡ የትዳርን ፡ ነገር ፡
ማሰብ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ የዛሬውን ፡ አዳር ።
ለሚመጣው ፡ ሁሉ ፡ በረዥሙ ፡ አስተውል ።
ያለንበት ፡ ጊዜ ፡ ማለፉን ፡ ካወቅኸው ፡
የኑሮህን ፡ ዘመን ፡ ለሥራ ፡ አድርገው ፡
በጣም ፡ ደስ፡ብሎኛል፡አሁን፡ ባስታወስከው ።

ገበሬው ፡ ውዲቱ ፡ የኔ ፡ ሚስት ፡ መከራዬ ፡ ነሽ ፡
በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ በማስተዋልሽ ።
ሌላውን ፡ ሐተታ ፡ እስቲ ፡ እናስቀምጠው ፡
ሞፈር ፡ ቀንበሩንም ፡ ከድብኝት፡አውጭው ፡
ለዘር ፡ ያልነው ፡ እህል ፡ እንዳለ ፡ ከጐታው ፡
እስቲ ፡ አውጭውና፡ ሥፍረሽ፡ ተመልከቺው።

የገበሬው፡ ሚስት ዘሩን፡ከየች፡በኋላ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ በጣም ፡ የሚያሰቅቅ፡
ሣይሻል ፡ አይቀርም ፡ የኔ ፡ ከዚህ ፡ መልቀቅ ።
ዛሬ ፡ ባለቤቴ ፡ ለዘር ፡ ሲዘጋጅ ፡
ጉዴ፡መፍላቱ፡ነው፡እንግዲህ፡ ምን፡ ይብጅ ።
እስቲ፡ ተነስቼ፡ ልሂድ፡እቤቶቼ፡ ለሁሉም፡ነገር፡
አልቅሼ ፡ ልናገር ፡ የቤቴን ፡ ችግር ፡
ስጡኝ ፡ ልበላቸው ፡ የሐምሌውን ፡ ዘር ፡
መቼም ፡ ወሰን ፡ የለው ፡ የኔ ፡ ማስቸገር ፡
ሰዓቱም ፡ ደረሰ ፡ ወቅቱ ፡ ነው ፡ የዘር ፡
አባቷንም ፡ ጠርታ ፡ ጀመረች ፡ ነገር ፡
እንባም ፡ ከዓይኖቿ ፡ ላይ ፡ ይፈልቁ ፡ ነበር ።
ስማኝ ፡ የኔ ፡ አባት ፡ ቸግሮኛል ፡ በጣም ፡
መቼም፡ሌላ፡ሰው፡ዘንድ፡ለመሄድ፡አልችልም።
ጊዜውም ፡ ሐምሌ፡ ነው፡ ወቅቱም ፡የዘር፡ነው፡
ባሌም ፡ በሬ ፡ ጠምዶ ፡ ገብቷል ፡ እማሳው ፡
ዛሬ ፡ ስለሆነ ፡ ዘሩ ፡ የሚዘራው ።

ከገመተራ ፡ አውጥቼ ፡ እንካ ፡ እምለው ፡ አጣሁ፡
አንተን ፡ ለማስቸገር ፡ ይኸውና ፡ መጣሁ ።

አባት ፡ እንባዋን
በኩታ ፡ እየጠረገ ፡

ተዋበች ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ አትዘኚ ፡
ያንቺም ፡ ቢሆን ፡ የባልሽን ፡ ችግር ፡ ንገሪኝ ።
አሁንም ፡ ለዛሬው ፡ ከሚያስፈልግሽ ፡
ወደ ፡ ቤት ፡ ሂጂና ፡ ለናትሽ ፡ ንገሪሽ ።
ከፈለግሽውም ፡ ዘር ፡ ሠፍራ ፡ አሥር ፡ ቁና ፡
በስልቻ ፡ አርጋችሁ ፡ ፩ ፡ ልጅ ፡ ጥሪና ፡
በቶሎ ፡ አድርሽለት ፡ አንቺም ፡ ሁኚ ፡ ደህና ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡
በፈገግታ ፡

እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ መልካሙ ፡ አባቴ ፡
ዕድሜ ፡ ያበድራት ፡ ለማማማም ፡ ለናቴ ፡
ፈጽሞ ፡ አረሳውም ፡ ካለሁ ፡ በሕይወቴ ።
አባባም ፡ እማማማም ፡ እስቲ ፡ ደህና ፡ ዋሉ ፡
በሮቹን ፡ አቁሞ ፡ ያ ፡ ገበሬው ፡ ባሌ ፡ ይጠ
ብቃል ፡ አሉ ።

ብላ ፡ ተሰናብታ ፡ ትሄዳለች ፡

ገበሬው ፡ በማሳ ፡
ውስጥ ፡

አምላክ ፡ ፈጣሪዩ ፡ ምን ፡ በድየህ ፡ ኖሯል ።
ዘር ፡ አምጭልኝ ፡ ብዩ ፡ ነግሬያት ፡ ነበረ ፡
ምን ፡ አግኝቷት ፡ ይሆን ፡ ድምጿ ፡ ተሰወረ ።
ከቤቴ ፡ ስወጣ ፡ ዘር ፡ አምጭልኝ ፡ ብዩ ፡ አ
ስታውሻታለሁ ፡
ቸግሯትስ ፡ እንደሁ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ ።
የዘንድሮ ፡ ችግር ፡ በጣም ፡ ተጫጭኗል ፡
ዋ ፡ ይሄ ፡ ቀን ፡ አልፎ ፡ አወጋው ፡ ይሆናል ።

እያለ ፡ በሃሳብ ፡ ሲናኝ ፡

ተዋበች ፡ ሚስቱ ፡

ወየው ፡ ጉድ ፡ ዘንድሮ ፡ በጣም ፡ ያስገርማል ፡

ይኸን ፡ ጊዜ ፡ ባሌ ፡ እኔን ፡ ይጠብቃል ፡
ጠባዩን ፡ አውቃለሁ ፡ በጣም ፡ ተበሳጭቷል ።

እያለች ፡ ከናትና ፡ አባቷ ፡ ቤት ፡ የወሰደ
ችውን ፡ ዘር ፡ ተሸክማ ፡ ትደርሳለች ።



ይህ ፡ ሥዕል ፡ ተዋበች ፡ ከቤቶቿ ፡ ዘንድ ፡ ዘር ፡ ይዛ ፡ ስትመጣ ፡ ያሳያል ።

ገበሬው ፡ በሩቅ ፡ ያያታል ፡

እሷ ፡ ናት ፡ መሰለኝ ፡ ያች ፡ ከርታታ ፡ ሚስቴ ፡
ለሰዎቹም ፡ ድኃ ፡ ለኔም ፡ እመቤቴ ።
የሷን ፡ መንከራተት ፡ በዐይኖቼ ፡ ሳይ ።
መሥራትም ፡ መኖርም ፡ ፈጽሞ ፡ አያስመ
ኝም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡
መከረዬ ፡ ሚስቴ ፡ የኔ ፡ አባባይ ።



እያለ ፡ ለብቻው ፡ ሲያስብ ፡ ተዋበች ፡ ዘር ፡ ይዛ ፡ ስትደርስ ፡ ገበሬው ፡ ቁምጣ ፡ ታጥቆ ፡ ሲያርስ ፡ ከነ ፡ በሮቹ ፡ በስዕል ፡ ይታያል ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡ ተዋበች ፡

እንደምን ፡ ውለሃል ፡ አንተ ፡ ግልቱ ፡ ባሌ ።
በጣም ፡ ጠቆርክብኝ ፡ ምን ፡ አገኘህ ፡ ዛሬ ።
በታዘዝኩት ፡ ሰዓት ፡ አውቃለሁ ፡ መቅረቴን ፡
እቤቶቼ ፡ ሄድኩኝ ፡ ልናገር ፡ ችግሬን ።
ያስቀመጥነው ፡ እህል ፡ እንዲሆን ፡ ለዘር ፡

ከቦታው ፡ አውጥቼ ፡ በቁና ፡ ብሰፍር ።
ባለመብቃቱ ፡ ነው ፡ እስከዚህ ፡ የቆየሁት ፡
ወዲያው ፡ ተነስቼ ፡ ሄድኩኝ ፡ አባቴ ፡ ቤት ።
በሙሉ ፡ ዘርዝሬ ፡ ችግራችንን ፡
ገልጬ ፡ አስረዳሁኝ ፡ ዘር ፡ እንዲሰጡን ።
ሃሳቤን ፡ በመስማት ፡ ቅርም ፡ አላላቸው ፡
መቸገራችንም ፡ ወዲያው ፡ ታወቃቸው ፡
ይኸው ፡ ሰጡኝ ፡ መጣሁ ፡ ይገኛ ፡ ከቤታቸው ።

ገበሬው ፡

ላረስነውም ፡ ማሳ ፡ ዘር ፡ ከተገኘለት ፡
አምላክ ፡ ካሰበልን ፡ እንዲህ ፡ ዕለት ፡ በዕለት ።
በኑሮአችን ፡ ሁሉ ፡ እንከን ፡ ካልገባን ፡
የቤታችን ፡ እህል ፡ ቀለብ ፡ ትሁነን ፡
ከጐመናችን ፡ ጋር ፡ እንዳንሞት ፡ እንዳንሸር ፡
እየቀማመስን ፡
ጊዜውን ፡ እንግፋው ፡ እየተሳሰብን ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡ ተዋበች ፡

ባሌ ፡ ዛሬ ፡ ጠዋት ፡ ምንም ፡ አልቀመሰ ፡
ሲደክም ፡ እንደዋለ ፡ ሰዓቱም ፡ ደረሰ ።
ለታረሰው ፡ ማሳ ፡ ለሚዘራውም ፡ ዘር ፡ እግ
ዜር ፡ ካሰበበት ፡
እቤት ፡ ካለው ፡ እሕል ፡ ትንሽ ፡ ቆንጥሬለት ፡
ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ብዬ ፡ ለራት ፡ ላድርስለት ።
በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ማሳውን ፡ ከዘራን
እቤት ፡ ያለችውን ፡ ለቀለብ ፡ አድርገን ፡
ለነሐሴው ፡ ሃሣብ ፡ በሰላም ፡ ያድርሰን ።

ብላ ፡ ለዘር ፡ ተዘጋጅታ ፡ ከነበረችው ፡ እህል ፡ አስናድታ ፡ እራት ፡ ይበላሉ ።

## ገበሬው ፡ በነሐሴ ።

አምላክ ፡ ካደረገኝ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አሣቢ ፡
ሚስቴንም ፡ ሳበሳጭ ፡ ብዬ ፡ ጓዳ ፡ ግቢ ።

ሰኔንና ፡ ሐምሌን ፡ በምንም ፡ አለፍነው ፡
እንግዲህ ፡ ንሐሴ ፡ ዋ ፡ ምን ፡ ሊበጀን ፡ ነው ።
ነፍሴን ፡ ባጠፋኋት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ መከራ ፡
ሰው ፡ ምን ፡ ይለኝ ፡ ባልል ፡ ይሉኝታ ፡ ባልፈራ
ነፍሴን ፡ በጄ ፡ አጥፍቻት ፡ ሥጋዬን ፡ በበላው
እንደኔ ፡ የተራበ ፡ የሰማይ ፡ አሞራ ።
ይኸው ፡ ስመለከት ፡ ወደፊት ፡ ሣይ ፡ አል
ቋል ፡ ቀለባችን ፡ የመክረሚያችን ፡
ዝም ፡ ብለን ፡ ቁጭ ፡ ነው ፡ የፍቅር ፡ ጫወታ ፡
እየተወያየን ፡ ።

የገበሬ ፡ ሚስት ፡ አይዞህ ፡ አትባባ ፡ አትደንግጥ ፡ በብዙ ፡
ምንም ፡ ቢሰፍርብን ፡ ችግር ፡ ከነጓዙ ።
ያላቸውም ፡ ሰዎች ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ቢያፌዙ ።
ማስወገጃው ፡ ዘዴ ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ ነው
እንጣላችሁም ፡ ቢል ፡ ታግሎ ፡ መከልከል ፡ ነው
ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ካገኘ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ነው ።
[ብላ ፡ መክራ ፡ ትንሽ ፡ የሽምብራ ፡ ቆሎ ፡
ቁርስ ፡ ትሰጠዋለች ፡ ቆርጥሞ ፡ ይነሳል ።

ገበሬው ፡ እስቲ ፡ ተነስቼ ፡ ወደ ፡ እርሻዬ ፡ ልሂድ ፡
ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ከሌለው ፡ አይወደውም ፡ ዘመድ
መቼም ፡ አይዘራ ፡ እንዲሁ ፡ ልዋት ፡
ጠላት ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ በኔ ፡ መታከት ፡
እንደናት ፡ እንዳባት ፡ የምትመክረኝ ፡ ሚስቴ
ቢኖረኝ ፡ ባይኖረኝ ፡ እሷ ፡ ብቻ ፡ እኮ ፡ ነች ፡
ለኔ ፡ ፀጋ ፡ ሀብቴ ።
በቃ ፡ አልሠራም ፡ ብዬ ፡ ትቼው ፡ ብመለስ ፡
መካሪዬ ፡ እሷ ፡ ናት ፡ ለችግሬም ፡ ልብስ ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እስክለይ ፡ አፈር ፡ እስክለብስ ፡

ድካማችሁ ፡ በቃ ፡ እስቲል ፡ ክርስቶስ ።
ጠንክሬ ፡ ልጣጣር ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡
ቀን ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል፡የሰው ፡ ልጅ ፡ መነሻው
ለሥራ ፡ ልጣጣር ፡ ስንፍናን ፡ አርቄ ፡
ከሰው ፡ በታች ፡ ሆኜ ፡ እንዳልቀር ፡ ወድቄ ።
ይኸውና ፡ ዛሬ ፡ ደመናው ፡ ቀለለ ፡
እንግዴህ ፡ ቢዘራ ፡ እንዴት ፡ በበቀለ ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ይሕ ፡ ሁሉ ፡ በፍጹም ፡ ምኞት ፡ ነው
ሽምብራና ፡ ስንዴ ፡ ዘሩ ፡ በብዙ ፡ ነው ።
እንዳሰቡት ፡ አይሆን ፡ ዋ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡
እኔማ ፡ ዘንድሮ ፡ አዝመራዬ ፡ ሁሉ ፡ ሐሳብ ፡
ብቻ ፡ ሆኗል ፡

የገበሬው ፡ ሚስት፡ አትበባ የኔ ፡ አካል ፡ ላለፉት ፡ ወራቶች ፡
አምላክ ፡ ካሰበልን ፡
እናባቃዋለን ፡ እንደምንም ፡ ብለን ።
ለዘር፡እንዲሆነን፡ከዚያ፡ከተሰጠን፡ከአሥሩቁና
አምላክ ፡ እስኪያወጣን ፡ ከዚህ ፡ ከፈተና ።
አምስቱ ፡ ሲዘራ ፡ ሌላው ፡ ተቀምጧል ፡
የጥራጥሬው ፡ እህል ፡ በሱ ፡ ይለወጣል ።
ስለዚህ ፡ አታስብ ፡ በጣምም ፡ አትፍራ ፡
ዘሩን ፡ ልያዝልህ ፡ ወስደንም ፡ እንዝራ ።

ገበሬው ፡ ክርስቶስ ፡ ሳይደግስ ፡ አይጣላም ፡ ሲሉ ፡
እሰማ ፡ ነበር ።
በጣም ፡ ተደስትኩኝ ፡ በሰጠሽኝ ፡ ምክር ።
ይህን ፡ የመሰለ ፡ ምክር ፡ ስትሰጭኝ ፡
እንግዲህ ፡ አላስብም ፡ ኩራት ፡ ተሰማኝ ።
አንቺ ፡ ደጊቱ ፡ ሚስቴ ፡ ስሚኝ ፡ ልንገርሽ ፡
ካየሁሽ ፡ ጀምሬ ፡ ረሐብ ፡ አይፈታሽ ፡

እንዴት ፡ ያለሺውን ፡ አምላክ ፡ ፈጠረሽ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካለሁ ፡ ዕድሜ ፡ ካበደረኝ ፡
እኔ ፡ ታዛኘሽ ፡ ነኝ ፡ ጊዜ ፡ የማይለውጠኝ ።
ይልና ፡ በሮቹን ፡ ጠምዶ ፡ የጥሬውን ፡
ዘር ፡ አምጭ ፡ ብሎ ፡ ይጌዳል ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡ እስቲ ፡ ልንማና ፡ ዘሩን ፡ ላድርስለት ፡
ይሄኔ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ የሚመለከት ።
ይቺን ፡ ዘራችንን ፡ ወስጄ ፡ ሰጥቼው ፡ ዛሬ ፡ ከተዘራ
እንግዴህ ፡ አለቀ ፡ ጣጣና ፡ መከራ ።
መስከረም ፡ እንግዴህ ፡ ዘር ፡ አያሳስብም ፡
እኛ ፡ ለራሳችን ፡ በጣም ፡ ብንራብም ፡
ዝም ፡ ብለው ፡ አያዩም ፡ አባባም ፡ እማማም ።
ጤንነቱን ፡ ሰጥቶን ፡ ስለ ፡ ኑሮአችንም ፡ ካደ
ረገን ፡ ሰላም ፡
በምግባችን ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ አንቸገርም ።
ብላ ፡ ዘሩን ፡ ታደርስለታለች ፡ ተቀብሎ ፡ ይዘራል ።

## ገበሬው ፡ ዘሩን ፡ ዘርቶ ፡ በመስከረም ።

ያቺ ፡ ደጓ ፡ ፍጥረት ፡ ባቀደችው ፡ ዘዴ ፡
ዛሬ ፡ ተገላገልኩ ፡ ሃሳቤን ፡ ከሆዴ ።
ሰኔን ፡ ሐምሌን ፡ ነሐሴን ፡ እንደምንም ፡ ወጣን
እንግዴህ ፡ መስከረም ፡ ተቀበለን ፡ መጣን ።
የወደፊቱን ፡ ሣይ ፡ ስመለከተው ፡
ካለፉት ፡ ወራቶች ፡ ይብሱ ፡ ይህ ፡ ነው ።
ባለፉት ፡ ወራቶች ፡ እኛም ፡ ባይኖረን ፡
እግዜር ፡ ባበቀለው ፡ ባቶ ፡ ጐመን ፡ ጉልበት
እስከዚህ ፡ ደረስን ።

ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡
ስጡን ፡ ብንላቸው ፡
አንጠራጠርም ፡ በመከልከላቸው ፡
አሁን ፡ ግን ፡ መስከረም ፡ ሹልክ ፡ ያለ፡ቀን፡ነው
የዘራውም ፡ ዘርቶ ፡ ቀሪው ፡ ቀለቡ ፡ ነው ፡
ወዴት ፡ ይደረሳል ፡ ዋኔ ፡ ምን ፡ ልሁነው ።

የገበሬው፡ ሚስት፡ አስብ ፡ ቢልህ፡ እኮ፡ነው፡ ከመጠንህ፡ በላይ
የበታችህን ፡ እንጂ ፡ የበላይህን ፡ አትይ ።
ካለፉት ፡ ወራቶች ፡ አይበልጥም ፡ ችግሩ ፡
ነገም ፡ ያው ፡ ሃሳብ ፡ ነው ፡ ቢገኝም ፡ ብድሩ ።
ዝም ፡ በል ፡ አካላቴ ፡ በጣም ፡ አትማረር ፡
መቼ ፡ ይታወቃል ፡ የክርስቶስ ፡ ነገር ፡
እንሥራ ፡ እንድከም ፡ በጣም ፡ እንጣጣር ፡
ለማንም ፡ አታዋይ ፡ ያገኘህን ፡ ችግር ፡
እገሌ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡
በጣም ፡ ይችኩላል ፡ ምሥጢር ፡ ለመዘርዘር ።
ሲሮጥ ፡ ታየዋለህ ፡ ያልከውን ፡ ሊናገር ።
ዝም ፡ ብሎ ፡ መቻል ፡ ነው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው
ጭራሽ ፡ አይገባም ፡ ችግር ፡ መንገር ፡ ለሰው ፡
ሲኖረው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሰው ፡ መወደጃው ፡
እስቲ ፡ ጠጣ ፡ ብለህ ፡ የዘራነውን ፡ ዘር ፡ ቡቃ
ያውን ፡ እየው ፡
እንኳን ፡ ለራሳችን ፡ በልተን ፡ ልንጨርሰው ፡
በዚሁ ፡ በአቅማችን ፡ እንተርፋለን ፡ ለሰው ።

እያለች ፡ ታጽናናዋለች ።

ገበሬው ፡ ወጣ ፡ ብዬ ፡ ባየው ፡ ቡቃያውም ፡ ቢያምር ፡
ሰው ፡ ከሞተ ፡ አይድንም ፡ ከገባ ፡ መቃብር ።
የሰው፡እኮ፡ሕይወቱ፡አንደኛው፡እህል፡ነው ፡

እህል ፡ ከሌለማ ፡ ኑሮስ ፡ ለምንድነው ።
እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ንጉሥንም ፡ ማክ
በር ፡ ሕግን ፡ መጠበቅ ፡
ዓይኖቼም ፡ የሚያዩት ፡ አተኩረው ፡ በሩቅ ፡
እህል ፡ሲበላ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚደምቅ ።
እሱማ ፡ ከሌለ ፡ ወድቄ ፡ መቅረቴን ፡ እርግጥ ፡
ነው ፡ አውቃለሁ ፡
አሁን ፡ ከወዴትስ ፡ ብድር ፡ አገኛለሁ ።
አሁን ፡ ሐብታሞቹ ፡ ብድር ፡ ቢጠየቁ ፡
ነገ ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ መመለሱን ፡ ሲያውቁ ፡
ገፍተህ ፡ አስወጣው ፡ ይላሉ ፡ በቊጣ ፡ እያነቁ ፡
ማግኘትም ፡ ማጣትም ፡ በኀይለ ፡ ሥላሴ ፡
መሆኑን ፡ ሳያውቁ ።
እያለ ፡ ጭብጥ ፡ ብሎ ፡ ያዝናል ።

የገበሬው ፡ ሚስ
ት ፡ እፊ ፡ ቁማ
ታጽናናዋለች ፡

ያልፍልናል ፡ አይዞህ ፡ በጣም ፡ አትጨነቅ ፡
በቊጣ ፡ አይቻልም ፡ የባሰ ፡ እንዳይመጣ ፡
አስቀድመህ ፡ ዕወቅ ፡
ስላለንበት ፡ ወር ፡ በጣምም ፡ አታስብ ፡
ይኸው ፡ ልንሾልከው ፡ ነው ፡ ግማሹ ፡ ደርሰ
ናል ፡ ስናስብ ፡ ስንሳብ ።
ገበሬና ፡ ወላድ ፡ ባምላክ ፡ አያማርርም ፡
ዛሬ ፡ ይስጠው ፡ ነገ ፡ የእድሉን ፡ አያውቅም ።
ተነስተህ ፡ ውጣና ፡ ወደበሮቻችን ፡ ቁጭ ፡
ብለህ ፡ አግጻቸው ፡
እባክህ ፡ አካሌ ፡ ፍጹም ፡ አትርሣቸው ፡
በነሱ ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ የምንመካው ።
በነሱ ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ የኛ ፡ መከበሪያ ፡
እነሱ ፡ አይደሉም ፡ ወይ ፡ የኛ ፡ መከበሪያ ፡

ክሌሉ ፡ እነሱ ፡ ደጀን ፡ ነን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ለች
ግር ፡ መሣሪያ ።
እንበደር ፡ ብንል ፡ ዋሶቻችን ፣ ናቸው ፡
ብንሸጣቸውም ፡ ገንዘባችን ፡ ናቸው ፡
እንግዲህ ፡ እወቀው ፡ ባሌ ፡ እንዘንጋቸው ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡

አዲስ ፡ ምክር ፡ ሰማሁ ፡ ገባ ፡ በደም ፡ ስሬ
ብልህ ፡ አዋቂ ፡ ነች ፡ ያቺ ፡ ሚስቴ ፡ ፍቅሬ ።
ስለ ፡ በሮቻችን ፡ ምክር ፡ ብትሰጠኝ ፡
ትዝ ፡ አለኝ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ ፀጸተኝ ።
በረሃብ ፡ አለንጋ ፡ እንዲህ ፡ ስንገረፍ ፡
ሐሣብ ፡ በላያችን ፡ እንደማዕበል ፡ ሲጐርፍ ።
ሁለት ፡ በሮች ፡ አሉን ፡ እርሻ ፡ የጨረሱ ፡
ሸጠን ፡ ብንሸምት ፡ አንደኛውን ፡ ከነሱ ።
እሱን ፡ ስንመገብ ፡ መከሩም ፡ ይደርሳል ፡
በመጀመሪያው ፡ ምርት ፡ መሰሉ ፡ ይተካል ።
ይህን ፡ ቶሎ ፡ ሄጄ ፡ ለሚስቴ ፡ ልንገራት ፡
በጣም ፡ ይሰማኛል ፡ እሷም ፡ እንደራበት ።
እኔን ፡ ለማፅናናት ፡ ያለችው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
በጣሙን ፡ ሕፃን ፡ ናት ፡ የትላንት ፡ ልጅ ።

ይልና ፡ ሚስቱን ፡ ጠርቶ ፡ ያማክራታል ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡

እቤትህ ፡ ከገባሁ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ፍጹም ፡ አልሰማሁም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወሬ ።
እንሥራ ፡ እንተካ ፡ እናብዛ ፡ ነበር ፡ ምኞታችን ፡
እናጥፋ ፡ ከሆነ ፡ ካለው ፡ ንብረታችን ፡
እኔም ፡ ቤቴ ፡ ልሂድ ፡ በል ፡ አንተም ፡ ደህና ፡
ሁን ፡
አበባው ፡ አብቦ ፡ ቡቃያው ፡ ዘርዝሮ ፡ ይኸው
እናያለን ፡

ነገም ፡ እንደሚደርስ ፡ በርግጥ ፡ እናምናለን ፡
እንኖራለን ፡ ካልክ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ተስማምተህ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ በጭራሽ ፡ ይቅርብህ ።
ይህንን ፡ ሐሣብክን ፡ ዛሬ ፡ ብቀበለው ፡
ለሚመጣውም፡ዘመን፡ያው፡መሆናችን፡ ነው ።

ብላ ፡ እየተቆጣች ፡ ትመክረዋለች ።

ገበሬው ፡ በፍርሐትና ፡ በሐዘን ፡

ይቅርታ ፡ አድርጊልኝ ፡ እባክሽ ፡ አካሌ ፡
በጣም ፡ ተሳሳትኩኝ ፡ ይኸውና ፡ ዛሬ ።
እንድትናደጂ ፡ ብዬ ፡ አላቀድኩትም ፡
ትቆጪያለሽ ፡ ብዬ ፡ ደግሞ ፡ አላሰብኩትም ፡
ባዘዝሽኝ ፡ እውላለሁ ፡ እንግዲህ ፡ ለሁሉም ።
ያንቺን ፡ መንከራተት ፡ መራብ ፡ መጠማትሽን
መድከምሽን ፡ ሣስበው ፡
እኔ ፡ የምመኘው ፡ መሞቴን ፡ ብቻ ፡ ነው ።
ማሪኝ ፡ ይቅር ፡ በይኝ ፡ በመጥፎው ፡ ሐሣቤ ፡
ሁኚ ፡ እንደ ፡ በፊቱ ፡ የዋሂቱ ፡ ርግቤ ፡
እርበኝም ፡ ብመጣ ፡ በጣም ፡ ትንገበግቤ ፡
በምክርሽ ፡ እጠግባለሁ፡በጣም፡ያርፋል ፡ልቤ ።

እያለ ፡ ገበሬው ፡ ሚስቱን ፡ ይቅርታ ፡ ይጠይቃታል ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡

ምክሬን ፡ ከተቀበልክ ፡ ሃሣቤም ፡ ከገባህ ፡
ይቅር ፡ አልቆጣም ፡ በቅድሙ ፡ ወሬህ ፡
እንግዲህ፡አዳምጠኝ፡አንድ፡ሃሣብ ፡ ልንገርህ ፡
ዛሬ ፡ የመስከረም ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ መሰለህ ።
ገፋነው ፡ አለፍነው ፡ ችግራችንን ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያውቀው ፡ ስለ ፡ ኑዳችን ፡
አበባንም ፡ ስናይ ፡ በጣም ፡ ተደሰትን ።
ከእንግዲህስ ፡ ወዲያ ፡ ለምንም ፡ አትፍራ ፡
ለፍሬ ፡ ከለልን ፡ የሠራነው ፡ ሥራ ፡

ስለ ፡ አበቃቀሉም ፡ በጣም ፡ ያስደስታል ፡ የዘ
ንድሮ ፡ አዝመራ ።

ገበሬው ፡ የዚያች ፡ የልጅ፡ ምክር ፡ምንኛ ፡ ጥልቅ ነው ፡
እውነትም ፡መስከረም ፡ዛሬ፡ ማለቂያው ፡ ነው ።
ሐገር፡ጐረቤቱ፡ እንዲህ፡ ሲያከብረን፡ ሲወደን፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ሣንገልፅ ፡ ችግራችንን ።
መራባችንንም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያውቀው ፡
ወደ ፡ ጥቅምቱ ፡ እሸት ፡ መሸጋገራችን ፡ ነው ።
እንግዲህ ፡ መስከረም ፡ አንተ ፡ ደጉ ፡ ቀን ፡
በደህና ፡ ያገናኘን ፡ እስቲ ፡ ደህና ፡ ሁን ።

## ገበሬው ፡ በጥቅምት ።

የገበሬው ፡ ሚስት፡ ይመስገን ፡ ፈጣሪ ፡ ለዚህ ፡ ያበቃን ፡
እንደ ፡ ብረት ፡ ምሰሶ ፡ ጽናቱን ፡ ሰጥቶን ።
የሐምሌን ፡ ቡቃያ ፡ በጥቅምት ፡ ካየነው ፡
ከእንግዲህስ ፡ወዲያ ፡ ብንሞትስ ፡ ምንድነው።
በሥላሴዎች ፡ ኃይል ፡ በሐምሌ ፡ ተዘርቶ ፡
በጥቅምት ፡ ወር ፡ አሣየን ፡ ጥሩ፡ፍሬ፡ አፍርቶ ።
በሁለታችን ፡ ድካም ፡ በየሱስ ፡ ቸርነት ፡
የሐምሌው፡ቡቃያ፡ለጥቅምት ፡ሆኗል፡ እሸት ።
እንግዲህ ፡ የኔ ፡ ባል ፡ በጣም ፡ እንዝናና ፡
የጥቅምቱን ፡ እሸት ፡ ባይናችን ፡ ካየነው ፡ ች
ግር ፡ የለምና ።
ያቺ ፡ የሐምሌ ፡ ወር ፡ ችግሯ ፡ እንዲያ ፡ ሲመር ፡
እሷስ ፡ አውቃው ፡ ኖሯል ፡ በጥቅምት ፡ መሆ
ኗን ፡ ማር ።
የሐምሌው ፡ ቡቃያ ፡ ለጥቅምት ፡ (ከ)ደረሰ ፡
እንግዲህ ፡ ለድሐ ፡ ችግር ፡ ተቃነሰ ።

**ገበሬው ፡**

ገበናዬ ፡ ሚስቴ ፡ ስሚኝ ፡ ላጫውትሽ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በመልካም ፡ ምክርሽ ፡
ሃሣቤም ፡ ተስፋፋ ፡ እኔም ፡ አካልሽ ።
እምቢ ፡ ብልሽ ፡ ኖሮ ፡ በፊት ፡ ስትመክሪኝ ፡
በዚህ ፡ በሽት ፡ ወራት ፡ እንዴት ፡ በፀፀተኝ ።
አሁን ፡ ግን ፡ በጥቅምት ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ የለ
እስቲ ፡ ወጣ ፡ ብለን ፡ እንይ ፡ እሸቱን ፡
በማየት ፡ ጠግበናል ፡ እንኳንስ ፡ በልተን ።
እንግዲህ ፡ አካሌ ፡ ችግሩን ፡ አልፈናል ፡
የጥቅምቱን ፡ እሸት ፡ ባይናችን ፡ አይተናል ።
በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡ ስለ ፡ ሐምሌው ፡ ዘሬ
መፈጠሬን ፡ ወደድኩ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሀገሬ ፡
ትንሽ ፡ ተሻሻለ ፡ ያሁሉ ፡ ችግሬ ።
ያቺ ፡ የሐምሌ ፡ ወር ፡ የተባለችው ፡
ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ እያፋጠነችው ፡
በጥቅምት ፡ መድኃኒት ፡ መሆን ፡ አበቃችው ።
እድላችን ፡ አምሯል ፡ እወቂው ፡ እንግዲህ ፡
ተነሽ ፡ እንራመድ ፡ እንበል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡
በኃይሉ ፡ አጽንቶናል ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ።

*ተባብለው ፡ ወደ ፡ እርሻው ፡ ማሳ ፡ ይሄዳሉ ፡*

**የገበሬው ፡ ሚስት በደስታ ፡**

ተመስገን ፡ ተመስገን ፡ የፈጠርከን ፡ ጌታ ፡
ሆነንም ፡ አልቀረን ፡ በፍጹም ፡ ከውታታ ።
ያለፈውን ፡ ችግር ፡ አሁን ፡ ሳስታውስ ፡
ምንም ፡ አልከፋንም ፡ በጣም ፡ አለን ፡ ደስ ፡
መንግሥቱም ፡ ትምጻ ፡ ስሙም ፡ ይቀደስ ፡
እስቲ ፡ እየው ፡ ባሌ ፡ የእህሉን ፡ መድረስ ።
ገብስ ፡ አተር ፡ ባቄላው ፡ ያነገበው ፡ ፍሬ ፡ ፩
እግር ፡ ነቅዬ ፡ ለመብላት ፡ ብሞክር ፡

እንኳንስ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አልጨርስም ፡ በወር ፡
ስለዚህ ፡ ለሥራ ፡ ጠንክረን ፡ እንጣር ።
ሰው ፡ ከሠራ ፡ አያጣም ፡ ካልሆነ ፡ ሰነፍ ፡
ዕወቅ ፡ አካሌዋ ፡ ሁሉም ፡ እንደሚያልፍ ።
ምድር ፡ አደራዋን ፡ እንዳትበላ ፡ አውቃለሁ ፡
ጠንክረህ ፡ እንድታርሥ ፡ ተቆጥቼሃለሁ ።
ላለፈው ፡ ነገሬ ፡ ተቀይመህ ፡ እንደሁ ፡ ይቅ
ርታ ፡ አድርግልኝ ፡
ጥፋት ፡ ቢኖርብኝ ፡ ከልብህ ፡ ተማክረህ ፡ ሳት
ደብቅ ፡ ንገረኝ ።



ትለውና ፡ ገበሬውና ፡ የገበሬው ፡ ሚስት ፡ ከደረሰው ፡ እሸት ፡ ነቅለው ፡ ተሸክ
መው ፡ በደስታና ፡ በፈገግታ ፡ እየተጨዋወቱ ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፡
ከነ ፡ እሸቱ ፡ በሥዕል ፡ ይታያሉ ።

ገበሬው ፡ ሚስቱን ፡ ጠርቶ ፡ ውቢቱ ፡ ተዋበች ፡ መልካሚቱ ፡ ፍሬ ፡
እንዴት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አመጣትሽኝ ፡ ዛሬ ።
በድየህ ፡ እንዲሆን ፡ መክረህ ፡ ከልቦናህ ፡
ንግረኝ ፡ ያልሺኝ ፡
ምን ፡ ተሰምቶሽ ፡ ይሆን ፡ በጣም ፡ አሰብኩኝ ።
ይልቁንም ፡ እኔ ፡ ነበርኩ ፡ የበደልኩሽ ፡
በዛሬው ፡ ነገርሽ ፡ በጣም ፡ አዘንኩብሽ ።
እንደ ፡ በደሉኝ ፡ ሲያውቅ ፡ ይቅርታ ፡ አልጠ
የቀም ፡ የማለትሽ ፡ እንደሁ ፡
ማረኝ ፡ መካሪዬ ፡ ፊትሽ ፡ ወድቄአለሁ ።
ለምን ፡ ሰው ፡ ሆንኩ ፡ ብዬ ፡ ከተቆጣሁማ ፡
መኖር ፡ ነበረብኝ ፡ ከአውሬዎች ፡ ጋር ፡ ውድማ ።
እንግዲህ ፡ እወቂው ፡ መረጃ ፡ ይሁንሽ ።
የሕይወቴ ፡ አበባ ፡ ሚስቴ ፡ ፍቅሬ ፡ አንቺ ፡ ነሽ
ይኸንን ፡ እውነት ፡ ቃል ፡ በርግጡ ፡ ስሰጥሽ ፡
ሌላውን ፡ ሐተታ ፡ እንደ ፡ ዱሮ ፡ ትተሽ ፡
ለጓዳሩ ፡ መከር ፡ ማሰብ ፡ ነው ፡ ያለብሽ ።
የገበሬው ፡ ሚስት ፡ ተቆጣህ ፡ መሰለኝ ፡ በዛሬው ፡ ነገሬ ፡
አንተ ፡ የኔ ፡ አልማገዝ ፡ ፍቅሬ ፡ ባሌ ፡ ክብሬ ።
እንግዲህ ፡ በሆዳችን ፡ ከሌለ ፡ ቅያሜ ፡
መለመን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ከፈጣሪ ፡ ዕድሜ ።
ስለ ፡ ቂም ፡ በቀሉ ፡ ከተገላለጽን ፡
እንመለስ ፡ እስቲ ፡ ስለ ፡ ሰብላችን ።
እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ የሰብሉ ፡ ስብሰባ ፡ በ
ጽሞና ፡ መንፈስ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ለምኖ ፡
ማሳጨድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጣም ፡ ጥንክር ፡ ሆኖ ።
የእህሉ ፡ አስተማጨድ ፡ ከልሆነ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት
ብቻዬን ፡ አጭጄ ፡ እችለዋለሁ ፡ ማለት ፡

ግብዝ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ነው ፡ የማይገባው ፡ ግምት ፡፡
ገበሬው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ እንዳልሽው ፡ እንደዚህ ፡ ካልሆን
መጨረስ ፡ አልችልም ፡ ብቻዬን ፡ ከሆን ፡
ሜዳ ፡ እንዳይቀርብን ፡ እንደተበተነ ፡፡
እስቲ ፡ እንደመከርሽኝ ፡ ተነስቼ ፡ ልሂድ ፡
ዳግም ፡ በዚህ ፡ ላስብ ፡ አያልቅም ፡ የኔ ፡ ጉድ ፡፡
ቢያገኙም ፡ ሃሣብ ፡ ነው ፡ ይሻላል ፡ ቢታጣ ፡
ቢሉት ፡ ቢሉት ፡ አያልቅ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጣጣ ፡፡
የሰብሉንም ፡ መድረስ ፡ ካየሁ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ያስጠላኝ ፡ ጀመረ ፡ እኔ ፡ መፈጠሬ ፡፡
ጠልቼ ፡ አይደለም ፡ ሰብሉ ፡ በመብዛቱ ፡
ስለበዛብኝ ፡ ነው ፡ ድካሙ ፡ በብርቱ ፡፡
ይልና ፡ አማጆች ፡ ልመና ፡ ይሄዳል ፡፡
የሐገሬ ፡ ሰዎች ፡ እንደዜ ፡ አዳምጡኝ ፡
የዘራሁት ፡ እህል ፡ አንድነት ፡ ደርሶብኝ ፡
እርዳታ ፡ ልመና ፡ ወደናንት ፡ መጣሁኝ ፡፡
ብድር ፡ ተመላሽ ፡ ነው ፡ ቅር ፡ እንዳይላችሁ
ባዘዛችሁኝ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኜ ፡ እደርሳለሁ ፡ እኔ
ም ፡ ወንድማችሁ ፡
እምቢ ፡ እንደማትሉኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ
ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ እጠብቃችኋለሁ ፡፡
እስካሁን ፡ እንግዴህ ፡ የኔ ፡ ልመና ፡ ነው ፡
አሁን ፡ ግን ፡ የቆምኩት ፡ መልሱን ፡ ለመስ
ማት ፡ ነው ፡፡
የተለመኑት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ በትሕትናህ ፡
አማጆች ፡ እንዲህ ፡ ስትናገር ፡ ፊታችን ፡ ቆመህ ፡
መታዘዝክን ፡ ስትገልጽ ፡ አንተም ፡ በተራህ ፡
በወሰንክልን ፡ ቀን ፡ ቆይ ፡ ተሰናድተህ ፡፡
ሲሉት ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ ይመለስና ፡ ለሚስቱ ፡ ይነግራታል ፡፡

ገበሬው ፡ አንቺ ፡ እንደ ፡ መከርሽኝ ፡ ሄጄ ፡ በጽሞና ፡
ከዚያ ፡ ላይ ፡ መንደር ፡ ቤት ፡ ያሉትን ፡ አራ
ሶች ፡ ጀመርኩኝ ፡ ልመና ፡፡
ኅዳር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ እንዲያጭዱልኝ ፡ መጥተው
በልዝብ ፡ አንደበት ፡ ቆሜ ፡ ብነግራቸው ፡፡
እንመጣለን ፡ አሉኝ ፡ ቅርም ፡ ሳይላቸው ፡፡

የገበሬው ፡ ሚስት ፡ እንግዴህ ፡ ፈቃዱ ፡ የሱ ፡ ይሁንና ፡
ለተባለው ፡ ሥራ ፡ ያድርሰን ፡ በደህና ፡፡
እስከዚያው ፡ ለደቦው ፡ የሚሆን ፡ እህል ፡፡
አቶ ፡ ሐብታሙን ፡ ሄደን ፡ አበድሩን ፡ ብንል
ወዲያው ፡ ይሰጡናል ፡ እንግዲህ ፡ ልንገርህ ፡
ለመረጃ ፡ ያህል ፡
ይህንን ፡ ያልሸበት ፡ ለምንድነው ፡ ብትል ፡
በማውቃቸው ፡ ነው ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ ሰብል ፡፡
ሰው ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ ከሰው ፡ ያላነሰ ፡
ሁሉም ፡ ይወደዋል ፡ እራሱን ፡ ከቻለ ፡ ልብ
ሱን ፡ ከለበሰ ፡፡
የኔን ፡ ቃል ፡ በእርግጡ ፡ አሁን ፡ እመንና ፡፡
ሄደን ፡ እንጠይቅ ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ሐብታሙ ፡
ይሰጡናልና ፡፡

ገበሬውና ፡ ሚስቱ ፡ ወደ ፡ ሐብታሙ ፡ ቤት ፡ ይሄዳሉ ፡፡

አሽከር ፡ ብቅ ፡ ይላል ፡ እናንት ፡ ምድናችሁ ፡ እዚህ ፡ የቆማችሁ
ሰው ፡ ለማስቆጣት ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ የምትገተሩት
ክቡር ፡ አቶ ፡ ሐብታሙ ፡ ትልቁ ፡ የኔ ፡ ጌታ
ያለመሰላቸው ፡ አይወዱም ፡ ጫዋታ ፡፡
ስለዚህ ፡ አትቁሙ ፡ ሂዱ ፡ ከደጃፉ ፡

ውርደት ፡ ሳትመጣ ፡ ወይም ፡ ሳትገፋ ።
እምቢ ፡ ካላችሁኝ ፡ አሳያችኋለሁ ።
በዚህ ፡ በያስኩት ፡ ሽመል ፡ አስፈግኋችኋለሁ ።

*እያለ ፡ ሲቆጣ ፡ ሐብታሙ ፡ ብቅ ፡ ይላል ።*

**አቶ ፡ ሐብታሙ ፡** ምንድነው ፡ ዘለፋ ፡ የምትጨቃጨቀው ፡
ይሄ ፡ ሁሉ ፡ ቁጣስ ፡ ከነ ፡ ማን ፡ ጋራ ፡ ነው ።

**ዘለፋ ፡** ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ እኚህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ዛሬ ፡
ጠዋት ፡ መጥተው ፡ እደጃፍ ፡ የቆሙ ፡
ሂዱ ፡ አትቆሙም ፡ ብል ፡ በፍጹም ፡ አይሰሙ ።
የበሩንም ፡ ደጃፍ ፡ አንለቅም ፡ ስላሉ ፡
በዚህ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ ብቅ ፡ ያሉ ።

*ሐብታሙ ፡ ጥራቸው ፡ ይላል ።*

*ዘለፋ ፡ ይጠራል ፡ ይገባሉ ፡* እናንት ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ከወደዬት ፡ መጣችሁ
ዛሬስ ፡ እዚህ ፡ መምጣት ፡ ምን ፡ አሳሰባችሁ ።

*ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ገብ ተው ፡ እጅ ፡ ይነሣሉ ፡* በዚህ ፡ ባአገራችን ፡ ብዙ ፡ አራሾች ፡ አሉ ፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ እናንተን ፡ ጨርሰው ፡ የማያክሉ
ያልኳችሁ ፡ አራሾች ፡ ባለብዙ ፡ በሮች ፡ ባለ
ርሥቶች ፡ ናቸው ።
ሰብሉን ፡ እንዳየሁት ፤ የናንት ፡ በለጣቸው ፡
አሁን ፡ ግን ፡ ምንድነው ፡ እዚህ ፡ ያመጣችሁ ፡
ገልጻችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ አትፍሩ ፡ አይዟችሁ ።

*ገበሬውና ፡ ሚስቱ ፡ ቆመው ፡ ገበሬው ፡ ችግራቸውን ፡ ይናገራል ።*

**ገበሬው ፡** ክቡር ፡ አቶ ፡ ሐብታሙ ፡ ይኸውና ፡ እንዳዩት
ብዙ ፡ ሰብል ፡ አለን ፡
አሁን ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ጥቂት ፡ የቸገረን ፡
ሰብሉ ፡ በመብዛቱ ፡ ሁለታችን ፡ አጭደን ፡ ስለ
ማያልቅልን ፡
በደቦ ፡ ለማጨድ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለመን ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ልምድ ፡ ሆኖ ፡ በቆየው ፡
ለሚያጭዱልን ፡ ሰዎች ፡ እንጀራና ፡ ጠላ ፡ ለ
ማስናዳት ፡ ነው ።
ስለዚህ ፡ ወደርስዎ ፡ በተስፋ ፡ መጥተናል ፡
በቸገረን ፡ ሁሉ ፡ ይረዱናል ፡ ብለን ።
እኛም ፡ ለወደፊት ፡ አውለን ፡ ሳናቆይ ፡ ቶሎ
እንመልሳለን ፡
እርስዎም ፡ ሣይቆጡ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ ሳያየን ።
አሁን ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ የምንመልስልዎ ፡
ሐብታሙ ፡ ይሙት ፡ ብለን ፡ ስንአስረዳዎ ፡
ይስጡን ፡ ግድ ፡ የለዎትም ፡ ቅርም ፡ አይበልዎ ።

**አቶ ፡ ሐብታሙ ፡** መረዳዳትማ ፡ መች ፡ ክፉ ፡ ነበር ፡
በጣም ፡ አሸላጊ ፡ ነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍጡር ።
አሁን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዲሁ ፡ እንደናንተ ፡
ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡
ተመልሰው ፡ ሄዱ ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ አጥተው
ይሄ ፡ የሆነበት ፡ ስሙኝ ፡ ምክንያቱን ፡
ባለፈው ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡
መጥተው ፡
በማልቀስ ፡ ነገሩኝ ፡ አጠገቤ ፡ ቆመው ።
እርበናልና ፡ ቶሎ ፡ የሚመለስ ፡ ስጠን ፡ ሁለ
ት ፡ ቁና ፡
እኔም ፡ ወዲያውኑ ፡ ከዚያ ፡ ከምታዩት ፡ ከት
ልቅ ፡ ጐተራ ፡
ይመለሳል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ በማድረጌ ፡
ሁለቱን ፡ ቁና ፡ እህል ፡ ሰጠኋቸው ፡ ዝቄ ፡
እነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ እንኳን ፡ የኔን ፡ እህል ፡ መል

ሰው ፡ ሊሰጡኝ
በክፉ ፡ ዓይናቸው፡ነው፡ሳያቸው፡የሚአዩኝ ፡
ይኸንን ፡ እህሌን ፡ ስለከለከሉኝ ፡
በመላው ፡ አካሌ ፡ ንዴቱ ፡ ተሰማኝ ።
በቅሎዬ ፡ እንድትጫን ፡ ወዲያው ፡ አዘዝኩ
ና ፡ ከችሎቱ ፡ ደረስኩ ፡
በግፍ ፡ መቀማቴን ፡ በደሌን ፡ ዘርዝሬ ፡ ጨር
ሼ ፡ ተናገርኩ ።
ይሄን ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ነገሩን ፡ መርምረው ፡
ተመለከቱና ፡
ሲሉም ፡ መለሱልኝ ፡ ወደህ ፡ ለሰጠኸው ፡
በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ዳኝነቱን ፡ ከፍለህ ፡
ፋይል ፡ ክፈትና ።
ከዚያማ ፡ ወዲህ ፡ የባሰው ፡ መጣ ፡
የፊቱን ፡ ሳላገኝ ፡ እንዲት ፡ ሌላ ፡ ላውጣ ።
ብዬ ፡ ተመልሼ ፡ ወደቤቴ ፡ መጣሁ ፡
የደከምኩበትን ፡ እህሌንም ፡ አጣሁ ።
እንዲህ ፡ እየሆነ ፡ ነው ፡ የተጨካከነው ፡
አሁን ፡ የምትሹት ፡ ስንት ፡ ቁና ፡ እህል ፡ ነው ።

ገበሬውና ፡ ሚስቱ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ አሁን ፡ እንደነገሩን ፡
እውነት ፡ አለዎ ፡ እርስዎም ፡
እንዲህማ ፡ ከሆነ ፡ አያቀባብርም ፡
ማግኘትና ፡ ማጣት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡
ተፈራራቂ ፡ ነው ፡
ዛሬ ፡ አስቀይሞ ፡ ነገ ፡ ምን ፡ ሊኾን ፡ ነው ፡
ስለዚህ፡ይህን፡ሁሉ፡አውቀን፡ነው፡የመጣነው ፡
አሁን ፡ ያስፈለገን ፡ ሀያ ፡ ቁና ፡ ጤፍ ፡ ነው ።

አቶ ፡ ሐብታሙ ፡ እንግዲህ ፡ ዘለፉ ፡ እወቅ ፡ ቤቱ ፡ ጠፉ ፡

ሀያውን ፡ ቁና ፡ ጤፍ ፡ ሰፍረህ ፡ ስጣቸው ፡
እኔ ፡ ጓሮ ፡ ልዞር ፡ አይኔም ፡ አያየው ።
ያለፈው ፡ እህል ፡ ነገር ፡ ሲከነክነኝ ፡
እኝህ ፡ የባሱት ፡ ደግሞ ፡ ከወዴት ፡ መጡብኝ ።
የሰዉንስ ፡ ነገር ፡ አይቼው ፡ በቅቶኛል ፡
የዚህን ፡ እህል ፡ ነገር ፡ አምላክ ፡ ያውቅልኛል ።

እያሉ ፡ ወደጓሮ ፡ ሲዞሩ ፡ አ ፡ ስ ፡ ይሰጣል ፡

**ገበሬውና ፡ የ ፡ ሚ ምስጋና ፡**

ሐብታሙ ፡ ጌታችን ፡
ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ጤናም ፡ ከርስዎ ፡ ይሁን ፡
ለዋሉልን ፡ ወሮታ ፡ ብድር ፡ መላሽ ፡ ያርገን ፡
የወሰድነውን ፡ እህል ፡ ቶሎ ፡ እንደምንመ
ልስ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ይሉና ፡ ወስደው ፡ ይሄዳሉ ፡

**አቶ ፡ ሐብታሙ ፡ ዘለፋን ፡ ጠርተው ያዋዩታል ፡**

እስቲ ፡ ረኸም ፡ እንጨት ፡ ቆርጠህ ፡ አምጣልኝ ።
የጐተራው ፡ እህል ፡ ብዙ ፡ አጥሮ ፡ እንደሆን
ማየት ፡ አለብኝ ።

ብለው ፡ ለከተው ፡ ያያሉ ፡ የጐደለውን ፡ ያህል ፡ ላሽከራቸው ፡ ያሳዩታል ።

ጉድ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ እንኳንስ ፡ በጁና ፡ የ
ኔን ፡ ቤት ፡ እህል ፡
ባይኑስ ፡ ማን ፡ ያየዋል ።
እህሌ ፡ ተመልሶ ፡ ባይኔ ፡ እስካየው ፡
ሥራዬም ፡ ይቅርብኝ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡
አምላክ ፡ ማልቀስ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**የገበሬው ፡ ሚስት ፡**

እንግዲህ ፡ የደቦው ፡ ቀኑ ፡ ተዳረሰ ፡
እኔም ፡ ተዘጋጀሁ ፡ ጠላውም ፡ ደረሰ ።
ጎዳርም ፡ ከገባ ፡ ፳ኛው ፡ ቀኑ ፡ ይኸውና ፡ ነገ ፡ ነው
ያንተ ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ይጥበሱልኝ ፡ ነው ።
አሁን ፡ ቶሎ ፡ ሂደህ ፡ በእየ ፡ ቤታቸው ፡

ለነገ ፡ መሆኑን ፡ ነግረህ ፡ አስታውሳቸው ፡
ሥራው ፡ የራሳችን ፡ መሆኑን ፡ ስታውቀው ፡
ይለምኑ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ ራሳቸው ፡ መጥተው ፡
ቶሎ፡ናልኝና፡የነገውን፡ሥራ፡ዛሬ፡እናዘጋጀው
መታጠብ ፡ አለበት ፡ መብያና ፡ መጠጫው ።
ዛሬ ፡ ዝግጅት ፡ አርገን ፡ ጠንቅቀን ፡ ካሳደርን ፡
ነገ ፡ ማቅረብ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ሌላ ፡ የለብን ።
አጫጆቹ ፡ መጥተው ፡ ሥራ ፡ ሲጀምሩ ፡ በወ
ደል ፡ ሽክና ፡ ጠላ ፡ እያስለመጡ ፡
አሸም ፡ በርቱልን ፡ ነው ፡ ቶሎ ፡ እንዳይወጡ ፡

ገበሬው ፡ እንዳዘዝሺኝ ፡ ሄጄ ፡ በሩጫ ፡ ገስግሼ ፡
ነግሬአቸው ፡ መጣሁ ፡ ለሁሉ ፡ አስታውሼ ።
እንዳልሺውም ፡ ሁሉ ፡ ጉድ ፡ ፈልቶብን ፡ ነበር ፡
በጭራሽ ፡ ረስተውታል ፡ ሄጄ ፡ ባልናገር ።
የነገው ፡ አጨዳ ፡ ዛሬ ፡ ይታየኛል ፡
ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሜዳ ፡ ክምር ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ።
ከኛውም ፡ ሃሣብ ፡ ጋር ፡ ያምላክ ፡ ተጨምሮ ፡
ሰብሉን ፡ ተሰብሳቢ ፡ ያድርገው ፡ ዘንድሮ ።

የገበሬው ፡ ሚ ተነስ ፡ ብቅ ፡ ብለህ ፡ እይ ፡ ምኑን ፡ ያንቀላፋሉ ፡
አጫጁ ፡ በሙሉ ፡ ወደማሳው ፡ ይጉርፋል ።
ንቃ ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ ሩጥ ፡ ድረስባቸው ፡
የሚጀምሩትን ፡ ወስደህ ፡ አሳያቸው ፡
እኔም ፡ እስክመጣ ፡ አንተ ፡ አትለያቸው ፡
አይዟችሁም ፡ እያልክ ፡ አደፋፍራቸው ፡
ማጨጃውም ፡ ሲደንዝ ፡ ሞርደህ ፡ ስጣቸው ፡
የዛሬውን ፡ አደራ ፡ ገላግሉኝ ፡ በላቸው ።
እኔም ፡ አሁኑኑ ፡ እደርስልሃለሁ ፡
ጠላውንም ፡ ይዤ ፡ በቶሎ ፡ እመጣለሁ ።

አጫጆን ፡ ማሳጨድ ፡ ቀላል ፡ ነው ፡ መንገዱ ፡
በፍ ፡ እየደለሉ ፡ መስጠት ፡ ነው ፡ ለሆዱ ፡
እወቅ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ቀድሜ ፡ ላስረዳህ ፡
በፊት ፡ የምትሠራው ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመህ ፡
ሽክና ፡ አድላቸው ፡ ሽማግሌ ፡ እያየህ ።
የሐገራችን ፡ ሰው ፡ መከበር ፡ ይወዳል ፡
በመስመሩ ፡ ሲሆን ፡ ሥራውንም ፡ ያበጃል ።
ትንሽ ፡ ትልቁንም ፡ በጣም ፡ እያከበርክ ፡
እነሱም ፡ ቢቆጡ ፡ አንተ ፡ እያሳለፍክ ።
የሚነግሩህን ፡ ሁሉ ፡ ታዛዥ ፡ ነኝ ፡ በላቸው ፡
ስለኛ ፡ ሲሰሩ ፡ ቅር ፡ እንዳይላቸው ።

ገበሬው ፡ አይዟችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ እኔ ፡ አለሁላችሁ ፡
በደከመው ፡ ተኩኝ ፡ ቅር ፡ እንዳይላችሁ ።
በዛሬው ፡ አጨዳ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡
እንግዲህ ፡ ባምላካችሁ ፡ እንቅልፍ ፡ ይወስ
ደኛል ፡
እንደናንተ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ ወንድሞች ፡ ሳሉኝ
እህሌ ፡ የማይታጨድ ፡ የሚጠፋ ፡ መስሎኝ ፡
ሳወጣና ፡ ሳወርድ ፡ ሳስብ ፡ ኖሬአለሁኝ ።
ዛሬማ ፡ በናንተ ፡ ሐሣቤን ፡ ጥያለሁ ፡
እኔም ፡ ለወደፊቱ ፡ ሰው ፡ እሆነዋለሁ ።
አሽም ፡ እሰይ ፡ ጐበዝ ፡ ቅቤ ፡ ጠጣ ፡ ሆዴ ፡
እዩት ፡ ሲያካልቡት ፡ እነ ፡ አንበሴ ፡ ወንዴ ።

እያለ ፡ የታጨደውን፡ ሲሰበስብ ፡ የገበሬው ፡ ሚስት ፡ ተዋበች ፡ ከጐረቤት፡ሌሎች ፡ ሴቶች ፡ ለምና ፡ ጋራ ፡ በሚአካክል ፡ ማድጋ ፡ ጠላና ፡ እንዲሁም ፡ ዳቦ ፡ ይዛ ፡ትደርሳለች ፡ የገበሬው ፡ ሚስት ፡ የማሳውን ፡ እህል ፡ መገባደድና ፡ የአጨዳውን ፡ እጥረት ፡ ስታይ ፡ እልል ፡ እልል ፡ ወንድ ፡ ብቻ ፡ ነውና ዛሬ ፡ የተሰበሰበው ።

እኔ ፡ ልቃጠለው ፡ ፀሐይ ፡ አቃጠላችሁ ፡
በባዶ ፡ ሆዳችሁ ፡ ተለበለባችሁ ፡
ደርሻለሁ ፡ ይኸው ፡ መልካሟ ፡ እህታችሁ ፡
ይሰማኝም ፡ ነበር ፡ ወሃ ፡ እንደጠማችሁ ፡
ወድጀን ፡ አይደለም ፡ እስካሁን ፡ የቆየሁ ።
ብቻዬን ፡ ስለሆንኩ ፡ ወዲህ ፡ ስል ፡ ወዲያ ፡
ስል ፡ ስላልሞላልኝ ፡
እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ይቅርታ ፡ አድርጉልኝ ፡
ከዚያች ፡ ከግራር ፡ ስር ፡ አረፍ ፡ እንበልና ፡
ጠላውን ፡ ጠጡልኝ ።



አጫጆቹ ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ተሰብስበው ፡ የዝሆን ፡ ጭንቅላት ፡ በሚያህል ፡
ሸክና ፡ ይኸን ፡ የገብስ ፡ ጠላና ፡ ዳቦውን ፡ ሲገምጡና ፡ ሲጋተሩት ፡ ይታያሉ ።

ከአማጆቹ ፡ አን ዱ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ መሚጠጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ይትርፋል ፡
ብለህ ፡
አይዞህ ፡ የኛ ፡ ወንድም ፡ አታስብ ፡ ላጨዳህ ።
እኛ ፡ ያንተ ፡ ጓደኞች ፡ እንኳንስ ፡ ላጨዳው
በብድር ፡ ለሚያድረው ፡
ለሞትም ፡ ቢጠሩን ፡ ልባችን ፡ አንድ ፡ ነው ፡
በሉ ፡ እንነሳ ፡ እንግባ ፡ ካጨዳው ፡
ሚስቱም ፡ ደስ ፡ ይበላት ፡ በዓይኗ ፡ ትየው ።
እንግዲህ ፡ እነጓዴ ፡ ስሙኝ ፡ ልንገራችሁ ፡
ብድግ ፡ ብድግ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ አጨዳችሁ ፡
ገበሬው ፡ በፈገግታ ፡ ተመስገን ፡ አምላኬ ፡ ዳግመኛ ፡ ፈጠርከኝ ፡
የአጨዳው ፡ ጣጣ ፡ ዛሬ ፡ ካለቀልኝ ።
እኚህ ፡ ገበሬዎች ፡ እንዳያያዛቸው ፡
እንኳን ፡ አጨዳና ፡ ጦርም ፡ አይፈታቸው ።
ነዱት ፡ አወረዱት ፡ እያውለበለቡት ፡
ከእንግዲህማ ፡ ወዲያ ፡ እንኳስ ፡ ሙሉ ፡ ቀን
አፍታም ፡ አያቆዩት ።
ባሰቡት ፡ አይሆንም ፡ አምላክ ፡ ሳይጨመር ፡
ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተፈጥሮ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሲኖር ።
የሰራውን ፡ ሥራ ፡ አልቆለት ፡ እስኪያይ ።
ቸልተኛ ፡ መሆን ፡ በፍጹም ፡ አያሻም ፡
መሥራት ፡ ነው ፡ መድከም ፡ ነው ፡ ለማግኘት
ሁሉንም ።
ያራት ፡ ሰዎች ፡ ሃሣብ ፡ ሁሉ ፡ በተለይ ፡ ነው ፡
ወታደር ፡ ጸሐፊ ፡ ደመወዙ ፡ በወር ፡ ነው ፡
የነጋዴም ፡ ትርፉ ፡ እለት ፡ በእለት ፡ ነው ፡
ገበሬ ፡ ግን ፡ ተስፋው ፡ በሩቁ ፡ ላመት ፡ ነው ።
በዚሁም ፡ መሐከል ፡ ብዙ ፡ ጣጣ ፡ አለበት ፡

ወይም ፡ ትል ፡ ወይም ፡ ውርጭ ፡ እህሉን ፡
ሲያጠፋበት ።
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲታወቅ ፡ ተመስገን ፡ ማለት ፡ ነው ፡
እግዜር ፡ ልስጠው ፡ ካለ ፡ ወዲያውን ፡ ቶሎ ፡ ነው ።
የገበሬው፡ሚስት፡ ለማረስ ፡ ለመዝራት ፡
አጭዶም ፡ ለመሰብሰብ ፡ ሰብስቦም ፡ ለመውቃት ፤
አድራሹ ክርስቶስ ፡ እሱ ፡ በኃይሉ ፡ ነው ፡
አውቃለሁ ፡ እውነት ፡ ነው ።
ካልሰራን ፡ ካልደከምን ፡ አርቀን ፡ ካላሰብን ፡
ባምሳሉ ፡ ተፈጥረን ፡ እርዱኝ ፡ እንድረዳችሁ ፡
ማለቱን ፡ እያወቅን ።
እንድንሠራበትም ፡ ዓይን ፡ እጅ ፡ እግር ፡ ሰጥ
ቶን ፡ ቀድሶ ፡ ባርኮናል ፡
እንግዲህ ፡ ለማግኘት ፡ ማሰብና ፡ መሥራት ፡
እወቀው ፡ ያሻናል ።
ስማኝ ፡ ባለቤቴ ፡ ሳየው ፡ ስገምተው ፡
ሁሉ ፡ ኃላፊ ፡ ነው ፡
ሰው ፡ ጉልበት ፡ እስካለው ፡
አስቦ ፡ መሥራት ፡ ነው ፡
የሰው ፡ እጅ ፡ ማየት ፡ ሁለተኛው ፡ ሞት ፡ ነው ።
አምናለሁ ፡ አውቃለሁ ፡ እንደሚታወስህ ፡
ባለፉት ፡ ወራቶች ፡ ያሁሉ ፡ ጭንቀትህ ።
አሁን ፡ ግን ፡ ተመልከት ፡ እስቲ ፡ ምን ፡ ይመ
ስልሐል ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡
ዛሬ ፡ እኛ ፡ ሆነናል ።
ስለዚህ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ለማግኘት ፡ በመሥራት
በመድከማችን ፡ ነው ።
ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ሰው ፡ ለመሆን ፡ የቻልነው

ገበሬው ፡ በውነት ፡ ለሚሠራ፡ አምላክም ፡ ቅርቡ ፡ነው ።
ተመስገን፡ነው፡እንጂ፡ ምን ፡መልስ፡ እሰጣለሁ ፡
አለኝ ፡ ብዩ ፡ አልኰራም ፡ ጨምሬ ፡ ለማግ
ኘት ፡ ቀጥዬ ፡ እጥራለሁ ።

አርሶ ፡ ማግኘት ፡ ሳለ ፡ ትልቁ ፡ አበልጻጊ ፡
ምንኛ ፡ ተጐዱ ፡ እነ ፡ ኪስ ፡ አውላቂ ።
ሌላውጋ ፡ እንኳ ፡ ቀርቶ ፡ ወደኔ ፡ ቢመጡ ፡
የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ አሁን ፡ በተሰጡ ።
አሁን ፡ ይኸው ፡ ነገ ፡ ታኅሣሥ ፡መግባቱ፡ ነው ፡
እህሉም ፡ ወደ ፡ አውድማ ፡ መሰብሰቢያው ፡
ወቅቱ ፡ ነው ፡
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የውቂያ ፡ ጊዜው ፡ ነው ።
ይህን፡ሁሉ፡ሥራ ፡አይችለውም፡ አንድ ፡ሰው ።
ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ አለ ።
ሰው ፡ ሥራ ፡ ጠልቶ ፡ ከሚንከራተት ፡
ጠንክሮ ፡ እየሰሩ ፡ ቆፍሮ ፡ መብላት ።
ከድህነት ፡ ለመራቅ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ብልሃቱ ፡
ሌት ፡ ከቀን ፡ ሳይሉ ፡ ቆፍሮ ፡ መብላቱ ።
የሰው፡ልጅ፡ከዶሮ፡በምን፡ምክንያት፡ያንሣል፡
እሱ ፡ እንኳ ፡ ባቅሙ ፡ ቆፍሮ ፡ ይበላል ።
ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ ሥራን ፡ የሚጠሉ ፡
ማታለል ፡ ማጭበርበር ፡ መስረቅ ፡ መቀማ
ትም ፡ ይሻላል ፡ እያሉ ።

የገበሬው፡ ሚስት ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተፈጥሮ ፡ የማያይ ፡ የኋላውን ፡
ዛሬም ፡ሰው፡ አይደለ፡ ለወደፊቱም ፡ አይሆን ።
ክቶ ፡ ሐብታሙ ፡ ዘንድ ፡ እህል ፡ ስንበደር ፡
ሲያትቱት ፡ ሰምተሃል ፡ ያንን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ።
በኛ ፡ እንደሌሎቹ ፡ ሳያማርሩብን ፡

ወስደን ፡ እንስጣቸው ፡ በቶሎ ፡ እህላቸውን ።
የሰው ፡ ልጅ ፡ ችግሩ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አይደለም ።
ዛሬ ፡ አገኘን ፡ ብለን ፡ ዝም ፡ ብንላቸው ፡
ይቀየምብናል ፡ ዓቃቤ ፡ መልአካቸው ።

ገበሬው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ተዋበች ፡ ጥሩ ፡ አስታውሰሻል ፡
በቅርብ ፡ ቀን ፡ ወስደን ፡ መመለስ ፡ ያሻናል ።
እስቲ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለሁለት ፡ እንማከር ።
ጠዋት ፡ ተነስቼ ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ ስወጣ ፡
ተገኘ ፡ ወርቁ ፡ የሚባል ፡ ሲቀናጣ ፡ መጣ ።
ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ወዲያው ፡ ከመድረሱ ፡
በጣም ፡ ይገርምሻል ፡ የእጅ ፡ አነሳሱ ።
እኔም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እብድ ፡ ሰው ፡ መስሎኛል
ለኔ ፡ እጅ ፡ መንሳቱ ፡ በምን ፡ ይገባኛል ።
እንዴት ፡ ዋልክም ፡ ሳልል ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ አየሁት ፡
ወዲያው ፡ መነጋገር ፡ ቀጠለ ፡ በፍጥነት ፡
ያስረዳ ፡ ጀመረ ፡ በለስላሳ ፡ አንደበት ።
በሰፊው ፡ ማረስዎን ፡ የእህሉ ፡ ክምር ፡ ይኸ
ው ፡ ይታየኛል ፡
የሀብትዎንም ፡ መሆን ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ነግሮኛል ።
ይህን ፡ በመስማቴ ፡ ሥራ ፡ ይሰጡኛል ፡ ስል
መጣሁኝ ፡ ከቤቴ ።
ስለዚህ ፡ ጌታዬ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ቢሰጡኝ ፡
በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ፍጹም ፡ ታዛዥዎ ፡ ነኝ ፡
ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ ከፈለገ ፡ ሐሰ
ትን ፡ ሳይጨምር ፡ በውነት ፡ እየሠራ ፡
ይኸው ፡ እንደርስዎ ፡ ይሆናል ፡ ቀብራራ ።
እኔም ፡ አሽከርዎ ፡ ሥራ ፡ ፈላጊ ፡ ነኝ ፡
መገኘት ፡ መጥፋቱን ፡ መልሱን ፡ እንዲነግሩኝ ።

ሲል ፡ እደጅ ፡ ቊሟል ፡
የዚህ ፡ የሰው ፡ መልሱ ፡ እንደምን ፡ ይሻላል ።
ልማከርሽ ፡ ብዬ ፡ ቆየኝ ፡ ብዬዋለሁ ፡
የማያሻን ፡ እንደሁ ፡ እንዲሄድ ፡ እነግረዋለሁ ።
የገበሬው ፡ ሚስት — የኛን ፡ ሐሳብ ፡ እሱ ፡ ቀድሞ ፡ በመናገሩ ፡
አዋቂ ፡ ይመስላል ፡ በተፈጥሮው ፡ ግብሩ ።
በዚህ ፡ በሃሳብህ ፡ በጣም ፡ እስማማለሁ ፡
ብቻህን ፡ ከመሆን ፡ አንድ ፡ የሚረዳህ ፡ ሰው
ብትቀጥር ፡ እወዳለሁ ።
በክርስቶስ ፡ ፈቃድ ፡ ሰው ፡ ለመሆን ፡ ከበቃን ፡
ከመቀጠር ፡ ወጥተን ፡ ለመቅጠርም ፡ ከቻልን ፡
ኃይሉ ፡ የሥላሴ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ተመስገን ።
ሄደህ ፡ ጥራውና ፡ ሁሉንም ፡ አስረዳው ፡
እህሉንም ፡ ሰብስቡት ፡ ያለውን ፡ ከየሜዳው ።
ገበሬው ፡ ተገኘን — እንግዲህ ፡ ተገኘ ፡ በጣም ፡ ሳትኰራ ፡
ጠርቶ ፡ ይነግረዋል — እኔን ፡ መስለህ ፡ ሥራ ።
ጠንክረህ ፡ መሥራት ፡ ነው ፡ ማግኘት ፡ እን
ድትችል ።
አንተም ፡ ሳትሠራ ፡ ለማግኘት ፡ አትቸኩል ።
ሰው ፡ ሣይሠራ ፡ ቢያገኝ ፡ ብዙ ፡ ግምት ፡ አለው ፥
መጠየቅ ፡ አለበት ፡ ከወዴት ፡ እንዳመጣው ።
አሁን ፡ የምመክርህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡
ወንድማማች ፡ ሆነን ፡ ነው ፡ አብረን ፡ ለመኖር ።
እንግዲህ ፡ ከዛሬው ፡ ጀምረህ ፡ ወደፊት ፡
የኔና ፡ ያንተ ፡ ነው ፡ እወቀው ፡ ይሄ ፡ ቤት ።
ደግሜ ፡ እማስረዳህ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡
እኔ ፡ አንተን ፡ ስቀጥር ፡ እኔን ፡ የቀጠረችኝ ፡
ተዋበች ፡ የሚሏት ፡ አንድ ፡ ሚስት ፡ አለችኝ ።

አሁን ፡ ስትገባ ፡ እሷን ፡ ታያታለህ ፡
ጥቂት ፡ ቀን ፡ ስትቆይ ፡ ከናትህ ፡ አብልጠህ
በጣም ፡ ትወዳታለህ ።

marriage is (financial) institution

ስለዚህ ፡ የሥራው ፡ መሬዋ ፡ እሷ ፡ ናት ፡
በማንኛውም ፡ ነገር ፡ እንዳታስቀይማት ።

ብሎ፡መክሮ፡ ተገኘ ፡ ወርቁን ፡ ይዞ፡ ገብቶ፡ ያስ
ተዋውቃታል፡ተገኘ፡እባላለሁ፡ብሎ ፡እጅ፡ ይነሳል

የገበሬው ፡ሚስት

እንግዲህ ፡ ተገኘ ፡ እኛ ፡ የምንፈልገው ፡
እያደሩ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ ነው ።
ድንገት ፡ ሳይታወቅ ፡ እኛ ፡ ብንበድልህም ፡
ከዚህ ፡ ቤት ፡ ተማረህ ፡ መውጣት፡ የለብህም ።
ብትቀየም ፡ እንኳ ፡ በኔም ፡ ቢሆን ፡ በባሌ ፡
አስቀድመህ ፡ ንገር ፡ ለሐገር ፡ ሽማግሌ ።
አሁን ፡ ይሄን ፡ ነገር ፡ ላንተ ፡ መናገሬ ፡
ስለሚታየኝ ፡ ነው ፡ ያለፈው ፡ ችግሬ ።
እንግዲህ ፡ ሳሳጥር ፡ ስናገር ፡ አልውልም ፡
አስብበትና ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡
ክርስቶስ ፡ ያስማማን ፡ እኛንም ፡ አንተንም ፡

ብላ ፡ መክራ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ይሄዳል ፡

ገበሬውና ፡ ተገኘ
ወደ፡ሥራ፡ሲሄዱ

እንግዲህ ፡ ተገኘ ፡ አምላክ ፡ ካገናኘን ፡
መጫኛ ፡ አምጣና ፡ ሄደህ ፡ ከቤታችን ፡
ከሜዳ ፡ ያለውን ፡ እህል ፡መሰብሰብ ፡ አለብን ፡
ወደ ፡ አውድማችን ፡
አሁን ፡ ከዚያ ፡ አንስተን ፡ አውድማ ፡ ካገባን ፡
ሲያሰኘን ፡መውቃት፡ ነው ፡ድካምም፡ የለብን ።
ያምላክ ፡ ሳይጨመር ፡ አይሆንም፡ሰው ፡ ባለው
በሜዳ ፡ያለውን ፡ እህል፡ ይኸው ፡ ሰበሰብነው።
መከሩም ፡ በሙሉ ፡ ተሰበሰበልን ፡

ይኸው ፡ ተቀነሰ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ አሳባችን ፡
የገበሬው፡ሚስት በቅን ፡ ከተሰራ ፡ በንጹሀ ፡ ልቦና ፡
እሱስ ፡ ቅርብ ፡ ኖሯል ፡ የማግኘት ፡ ጉዳና ።
ወደኋላ ፡ ሳየው ፡ የነበርንበትን ፡
የዛሬውን ፡ ስናይ ፡ አሁን ፡ ያለንበትን ፡
ሰው ፡ እንዴት ፡ ይጠላል ፡ ሥራና፡ ሕብረትን ።
ተወዳጁ ፡ ባሌ ፡ እስቲ ፡ ወደ ፡ አውድማው ፡
ትኩር ፡ ብለህ ፡ እየው ።
ጠንክሮ ፡ በመሥራት ፡ በመጣጣር ፡ ነው ፡
ይኸን ፡ ሁሉ ፡ እህል ፡ ማግኘት ፡ የቻልነው ።
ትላንትና ፡ ጠዋት ፡ አንተና ፡ ተገኘ ፡ ለሥራ
ሄዳችሁ ፡
እህሉን ፡ ስታግዙ ፡ ወደ ፡ አውድማችሁ ።
አፈራሁ ፡ በትዕግሥት ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡
ሰተት ፡ ብላ ፡ መጣች ፡ እዚህ ፡ እኛ ፡ ቤት ።
እኔም ፡ በትሕትና ፡ ተቀበልኳትና ።
የመጣችበትን ፡ ጉዳዩን ፡ ጠየቅኋት ፡
እሷም ፡ ስትናገር ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ እያላት ።
ሥራ ፡ በማጣቴ ፡ ስለቸገረኝ ፡ ነው ፡
እናንተ፡ ስላላችሁ ፡ ሥራ፡እንድትሰጡኝ፡ነው።
ለዚህ ፡ ነው ፡ አመጣጤ ፡ የማላገኝ ፡ እንደሁ ፡
ልመለስ ፡ እቤቴ ፡
መልሱን፡ ቶሎ፡ ይንገሩኝ፡ ክብርት ፡ እመቤቴ ።
እኔም ፡ የሷን ፡ ንግግር ፡ ሁሉን ፡ ተቀብዬ ፡
ሸኘቼ ፡ ሰደድኳት ፡ ነገ፡ ጥርᎏ ፩ ተመለሽ፡ ብዬ ።
ይህን ፡ ያደረግሁት ፡ ካንተ ፡ ልማከር ፡ ነው ፡
የማይሆን ፡ ከሆነ ፡ የለም ፡ እንድላት ፡ ነው ።
እንግዲህ፡ሐብቴ፡ሚስቴ፡አድምጭኝ፡ልንገርሽ

ብሆዴ ፡ ያለውን ፡ አንድም ፡ ሳልደብቅሽ ።
ተገኘን ፡ ከቀጠርን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
መሥራት ፡ አቅቶታል ፡ ፈጽሞ ፡ የደም ፡ ስሬ ።
ይህ ፡ የሆነበትን ፡ ምክንያቱን ፡ ልንገርሽ ፡
እኔ ፡ ረዳት ፡ ሳገኝ ፡ አንቺ ፡ በማጣትሽ ፡
መጥቶ ፡ ፊቴ ፡ ይቆማል ፡ ሥራውና ፡ ድካምሽ ።
ስለዚህ ፡ ቀጠሯት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡
እኔም ፡ ከኃሣቡ ፡ ይቀነስልኛል ።

የገበሬው ፡ ሚ ፡ ከ ፡ አፈ ፡ ጋ ፡ ስት ነጋገር ፡
እንደምን ፡ አድረሻል ፡ መሰሏ ፡ ወገኔ ፡
ትላንትና ፡ ማታ ፡ እዚህ ፡ እንደመጣሽ ፡
እርግጥ ፡ ነው ፡ ይሰማኛል ፡ ቀጠሮ ፡ መስጠቴን ፡
ዛሬ ፡ እንድትመለሽ ።
አንቺን ፡ ለማጉ ላት ፡ አይደለም ፡ እህቴ ፡
ይወቀው ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ጉዳዩን ፡ ባለቤቴ ።
የመጣሽበትን ፡ ጉዳዩን ፡ ብነግረው ፡
ይሁን ፡ ብሎ ፡ ፈቅዷል ፡ በፍጹም ፡ ሳይከፋው ።
ስለዚህ ፡ እንግዲህ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ብትኖሪ ፡
እስከ ፡ መጨረሻው ፡
እኔም ፡ እህትሽ ፡ ነኝ ፡ እሱም ፡ ወንድምሽ ፡ ነው ።
አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ ስሚኝ ፡ አስቀድመሽ ፡
እስካሁን ፡ እኔን ፡ እንጂ ፡ ባሌን ፡ ስላላየሽ ።
አሁን ፡ ቶሎ ፡ ይመጣል ፡ መግቢያ ፡ ሰዓቱ ፡ ነው ፡
የኛ ፡ አሳዳሪ ፡ እውቂው ፡ እሱ ፡ ነው ።
አመሉም ፡ ያማረ ፡ ጥሩ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ።

ገበሬው ፡
ተዋበች ፡ አዳምጭ ፡ እኔና ፡ ተገኘ ፡ ትልቅ ፡
ጀብዱ ፡ ሠራን ፡
የአቶ ፡ ሐብታሙን ፡ እህል ፡ ወስደን ፡ ሰጥተን ፡
መጣን ።

እህሉን ፡ ስሰጣቸው ፡ በጣም ፡ ተደስተው ፡
መጥተው ፡ ጉንጬን ፡ ሳሙኝ ፡ ካልጋቸው ፡
ተነስተው ።
የምርቃቱማ ፡ ስንቱ ፡ ይታወሳል ፡
ከብዙው ፡ አንደኛው ፡ ይህ ፡ ይታወሰኛል ።
በዚያ ፡ ባላችሁበት ፡ በሰጣችሁኝ ፡ ቃል ፡ በለ
መጉደላችሁ ፡
ፈጣሪ ፡ አምላኬ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ይስጣችሁ ።

የገበሬው ፡ ሚ ፡ አፈራሁ ፡ በትዕግሥት ፡ የተባለችዋ ፡ ሴት ፡
ትላንት ፡ የነገርኩህ ፡ ሥራ ፡ ጀምራለች ፡
ካንተም ፡ ለመተዋወቅ ፡ ይኸውና ፡ ቆማለች ።

ገረድ ፡ እጅ ፡ ትነሳና ፡ አፈራሁ ፡ በትዕግሥት ፡ ማለት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡
ይወቁኝ ፡ ጌታዬ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሬ ፡ ገረድዎ ፡ ነኝ ።
(ትለዋለች) ፡

ገበሬው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አንቺ ፡ በመሆንሽ ፡
እንግዲህ ፡ በሥራ ፡ ሚስቴን ፡ እየረዳሽ ።
እኛ ፡ የውጭውን ፡ እናንተ ፡ ከቤት ፡
ይህ ፡ ለማ ፡ ያጠፉ ፡ እየተባባላችሁ ፡
ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ ነው እንግዲህ ፡ ያለባችሁ ።
ሚስቴም ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ናት ፡ ወዲያውም ፡
ወገንሽ ፡
ትለምጃለሽ ፡ አይዞሽ ፡ ቅርም ፡ እንዳይልሽ ፡
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እወቂው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ቤትሽ ።

የገበሬው ፡ ሚ ፡ ምነው ፡ ሥራ ፡ ፈታን ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ በዛ ፡
ደከም ፡ ደከም ፡ እያልን ፡ ሥራውም ፡ ተረሣ ።
ትላንት ፡ ትእዛዝ ፡ መጥቷል ፡ በመልከኛው ፡
በኩል ፡
በየካቲት ፡ ወራት ፡ ስለ ፡ መሬታችን ፡ ግብር ፡
እንድንገብር ፡

እንግዲህ ፡ አፋጥኑት ፡ በሉ፡ጠንክር፡ጠንክር፡
ቀኑ ፡ ሳይተላለፍ ፡ ወስደን ፡ እንድንገብር።
እርስትን ፡ በጅ ፡ ይዞ ፡ ግብርን ፡ መከልከል ፡
እየተጠቀሙ ፡ በሚሰጠው ፡ አበል ።
መንግሥትን፡አይደለም፡ራስን፡ነው፡መበደል።
ባለሥልጣኖችም ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አይላቸው፡
በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ካልገበሩላቸው ።
አሁን ፡ ችላ ፡ እያልን ፡ ብናዘገየው ፡
ቃሥረን ፡ መክፈሉን ፡ ፍጹም ፡ አትዘንጋው።
ተከብረን ፡ በማዕረግ ፡ ብንከፍል ፡ ይሻለናል ፡
በመገደድም ፡ ቢሆን ፡ መች ፡ ይቀርልናል ።
ለኛውም ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ በጣም፡ ያሳፍራል፡
ለራስ፡መሬት፡ግብር፡ሰው፡እንዴት፡ይወቀሳል፥
ገበሬው ፡ እንደምን ፡ ውለሻል ፡ አንቺ ፡ የኔ ፡ ጥንክር ፡
በቃልሽ ፡ መሠረት ፡ በመከርሺኝ ፡ ምክር ፡
ከፍዬ ፡ መጣሁኝ ፡ የመሬቱን ፡ ግብር ።
ባለተስፋ ፡ ሰዎች ፡ ነን፡እንግዲህ፡አንጠርጥር።
ዳኛ ፡ ይሁን ፡ መልከኛ ፡ ወይም፡ ጭቃ፡ ሹም፡
በምንም ፡ ምክንያት ፡ አይደርስብንም ።
የመሬታችንን ፡ ግብሩንም ፡ ይኸው ፡ ገበርን ፡
በሰላም ፡ ጨረስነው ፡ የየካቲትንም ፡ ወር ።
እንግዲህ ፡ መጋቢት ፡ የውቂያ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡
ከተገኘ ፡ ጋራ ፡ ቃጠቅ ፡ እንበልና ፡ እንጀም
ራለን ፡
የሚያዝያው ፡ በልግ ፡ እርሻ ፡ ቶሎ ፡ ሳይደር
ስብን ።
ተዋበች ፡ አንቺና ፡ አፈራሁ ፡ ገረድሽ ፡ ሁለት
ሆናችሁ ፡

ጐተራ ፡ አዘጋጁ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ብላችሁ ።
ለሚአቅታችሁም ፡ ለኛ ፡ እንድትነግሩን ፡
እንረዳችኋለን ፡ አንዳንዴ ፡ እየመጣን ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡
እናንተ ፡ ወንዶቹ ፡ ጠንክሩ ፡ በሥራችሁ ፡
በኛ ፡ በሴቶቹ ፡ ቅርም ፡ አይበላችሁ ።
በኛ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ተዘጋጅቷል ፡
ይልቁን ፡ እናንተ ፡ ለሚያስፈልጋችሁ ፡
እንድትነግሩንና ፡ እንድንረዳችሁ ።
ምንም ፡ ሴቶች ፡ ብንሆን ፡ ግዴለም ፡ አትናቁን ፡
ያለእኛ ፡ እንደማይሆን ፡ እወቁት ፡ እቅጩን፤
በማንኛውም ፡ በኩል ፡ ረዳቶቻችሁ ፡ ነን ።

ገበሬው ፡
የውድማውም ፡ ክምር ፡ በሙሉ ፡ ተወቅቷል ፡
ሥራውም ፡ እንደ ፡ ሰንጠረዥ ፡ በታ ፡ በታ
ውን ፡ ይዟል ፡
የሚያዝያውም ፡ ደመና ፡ ይኸው ፡ ተንጠል
ጥጓል ፡
አሁን ፡ ይዘንብና ፡ ለበልግ ፡ ያሳምራል ፡
ጤፉን ፡ ስንወቃ ፡ ጭዱን ፡ ከምረናል ፡
ለገበሬዎቻችንም ፡ ቀለብ ፡ ይሆናቸዋል ።
እንግዲህ ፡ እናስብ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እርሻችን ፡
በሚያዝያ ፡ ዘንበ ፡ ምድሩን ፡ ካራሰልን ፡
ማሽላ ፡ በቆሎ ፡ ነው ፡ የመጀመሪያችን ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡
ሰማኸኝ ፡ ወይ ፡ ባሌ ፡ እናትና ፡ አባቴን ፡ ብዙ
ጊዜ ፡ ሆነኝ ፡ ሄጄ ፡ ሳላያቸው ፡
ፈድቃህ ፡ ይሁንና ፡ ልምጣ ፡ ጠይቄአቸው ፡
እወቅ ፡ ታዝበውናል ፡ ይሄኔ ፡ በሆዳቸው ፡
በዚያ ፡ በችግር ፡ ቀን ፡ በውነት ፡ ረድተውናል ፡
ዛሬ ፡ አግኝተን ፡ ብንቀር ፡ ያማርሩብናል ።

ገበሬው ፥ እኔም ፡ አስቤአለሁ ፡ አንቀርም ፡ እንሄዳለን ፡
ከስንዴም ፡ ከጤፉ ፡ ነጭ ፡ ነጩን ፡ መርጠን ፡
ከሰባውም ፡ ሙክት ፡ ላክፋያቸው ፡ ይዘን ።
እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ስላልጠየቅናቸው ፡
ማሩን ፡ እንላለን ፡ ወድቀን ፡ ከፊታቸው ፡
እንዲመርቁንም ፡ በንጹሕ ፡ ልባቸው ፡
ከኛም ፡ እንዳይለይ ፡ ረድኤታቸው ።
እወቂ ፡ እናት ፡ አባት ፡ በልጁ ፡ አይጨክንም ፡
ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ ይቅር ፡ እንደሚሉንም ።

የገ ፡ ሚ ፡ ቀገኘ ፡ የጾሙ ፡ መፈቻ ፡ ስለተዳረሰ ፡

ወ ፡ ትጠራለች ፡ ካሉት ፡ ሙክቶች ፡ ውስጥ ፡ ፩ኛውን ፡ መርጠህ ፡
እንድትቀልበው ፡ አደራህን ፡ እባክህ ።
ይኸውም ፡ የነገርኩህ ፡ ተቀላቢው ፡ ሙክት ፡
የሚሄድ ፡ ነውና ፡ እናት ፡ አባቴ ፡ ቤት ፡
የያዙትንም ፡ ጾም ፡ የሚፈስኩበት ።
ሁለተኛም ፡ ደግሞ ፡ ሄደህ ፡ ጐተራውን ፡
እየውና ፡ ከፍተህ ፡
ከስንዴም ፡ ከጤፉ ፡ ያማረውን ፡ አይተህ ፡
አስር ፡ አስር ፡ ቁና ፡ ባይነቱ ፡ ለይተህ ፡
በስልቻ ፡ ገብቶ ፡ ይቆይ ፡ አዘጋጅተህ ብላ ፡ ታዘዋለች ፡

ተገኘ ፡ ወርቁ ፡ እሺ ፡ እመቤቴ ፡ ፍጹም ፡ ታዛዥዎ ፡ ነኝ
የታዘዝኩትንም ፡ ቶሎ ፡ ፈጻሚ ፡ ነኝ ፡
ካሉት ፡ ሙክቶች ፡ ውስጥ ፡ ፩ኛው ፡ ተመ
ርጦ ፡ ይቀለብ ፡ ስላሉኝ ፡
ስለዚህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ትንሽ ፡ ቅር ፡ የሚለኝ ።
ያሉንን ፡ ሙክቶች ፡ አሁን ፡ አብረን ፡ ሄደን ፡
አንደዜ ፡ ቢያይዋቸው ፡

ተኝተው ፡ ነው ፡ የሚውሉት ፡ መሄድ ፡ አቅ
ቷቸው ።
እንዲህም ፡ ለመወፈር ፡ ለመስባት ፡ የቻሉት ፡
ምክንያቱን ፡ ላስረዳ ፡ ይስሙኝ ፡ ልንገርዎት ፡
በግም ፡ ሆነ ፡ ፍየል ፡ ቀለብ ፡ ሳይቀለብ ፡ መስ
ባት ፡ የሚችለው ፡
በጠባቂው ፡ እረኛ ፡ ሃሳቡን ፡ ጥሎ ፡ ነው ።
አሁን ፡ እንዳዘዙኝ ፡ አግብቼ ፡ ብቀልብ ፡
ፈንድተው ፡ ይሞታሉ ፡ አይሆኑንም ፡ ገንዘብ ።
እንደታዘዝኩትም ፡ እህሉንም ፡ ለመምረጥ ፡
ጐተራውን ፡ ከፍቼ ፡ ብመለከተው ፡
የሐገራችን ፡ መሬት ፡ የአፈራችው ፡ እህል ፡
አንዱም ፡ የሚመረጥ ፡ የሚቀር ፡ የለው ፡
ለዓይንም ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ሁሉም ፡ የአማረ ፡ ነው ፡
በኔ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ዝግጁ ፡ ነው ።
በቀረው ፡ ተክተን ፡ በጐደለው ፡ ሞልተን ፡
ለታሰበው ፡ ሰዓት ፡ ክርስቶስ ፡ ያድርሰን ፡
ይልና ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ይሄዳል ፡

የገበሬው ፡ ሚስት ፡ አፈ ፡ በት ፡ ትጠራለች

አሁን ፡ ካንቺ ፡ በፊት ፡ ተገኘን ፡ ጠርቼ ፡
በሱ ፡ በኩል ፡ ላለው ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንዲቆይ ፡
ነገርኩ ፡ አስረድቼ ።
አንቺም ፡ ለበኩልሽ ፡ ማወቅ ፡ ስላለብሽ ፡
ልንገርሽ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ የጠራሁሽ
አሁን ፡ ቶሎ ፡ ሄደሽ ፡ ተገኘን ፡ ፈልገሽ ፡
ነጩን ፡ ስንዴ ፡ መርጠ ፡ ንገሪው ፡ እንሰዲጥሽ ፡
ይኸንንም ፡ ስንዴ ፡ በመልካም ፡ ሁናቴ ፡ በደ
ንብ ፡ ፈትገሽ ፡
አድርቀሽ ፡ ስጭውና ፡ አስፈጭቶ ፡ ያምጣልሽ ።

ይኸው ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ የመፈሰኪያው ፡ ትን
ሣኤው ፡ ቀን ፡ ነውና ፡
ዝግጅት ፡ ዝግጅት ፡ በይ ፡ ጠንቀቅ ፡ በይና ።
የሚጋጋረውም ፡ የዶሮ ፡ ዳቦ ፡ ነው ፡
እሱም ፡ የሚሄደው ፡ ለናት ፡ አባቴ ፡ ነው ፡
እሺ ፡ የኔ ፡ እመቤት ፡ ሲያዙኝስ ፡ ምን ፡ ከፍቶኝ
አሁን ፡ ተነስቼ ፡ አዘጋጅቀዋለሁኝ ።
ይፍቀዱልኝና ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ልናገር ፡
ካልፈቀዱልኝም ፡ የታዘዝኩበትን ፡ ሥራዬን
ልጀምር ፡

እመቤት ፡ ትፈቅዳለች ።

ገረድ ፡ ሲሉም ፡ አዘውኛል ፡ የዶሮውም ፡ ዳቦ ፡ በቶ
ሎ ፡ እንዲጋገር ።
ዶሮ ፡ ዳቦ ፡ ሲባል ፡ ዓይነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡
አሁን ፡ እምጋግረው ፡ የትኛው ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

የገበሬው ፡ ሚስት ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ጥያቄ ፡ አቅርበሻል ፡
እኔ ፡ እንኳ ፡ ብሳሳት ፡ አንቺ ፡ አስታውሰሻል ።
እናትና ፡ አባቴ ፡ ዕድሜአቸው ፡ ብዙ ፡ ነው ።
ሌት ፡ ከቀን ፡ በጸሎት ፡ እንቅልፍ ፡ በማጣት ፡
ልባቸውም ፡ ደክሟል ፡ በጸሎት ፡ ብዛት ።
በዶሮ ፡ አልጫ ፡ ብትጋግሪላቸው ፡
እመኚ ፡ በጣሙን ፡ እንደ ፡ ሚሻላቸው ።

ገረድ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እመቤቴ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይስጥልኝ ፤
ለጥያቄዬ ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ ስላስረዱኝ ።
እስቲ ፡ ልሂድና ፡ ሥራዬን ፡ ልጀምር ፡ ገብቼ ፡
ወደጓዳ ፡
ምጣዱንም ፡ ልጣድ ፡ ቤቱን ፡ ላጸዳዳ ፡

ፈጠን ፡ ፈጠን ፡ ላርገው ፡ ቶሎ ፡ ላሰናዳ ።
የተባለው ፡ ዳቦ ፡ በዶሮ ፡ አልጫ ፡ ይጋገር ፡ ካሉን
ይህን ፡ ነጭ ፡ ድፎ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ብለን ፡
እሳትም ፡ እንዳያንሰው ፡ አንቃቅተን ፡ አስምተን
ከተባለው ፡ ቦታ ፡ ነገ ፡ እንወስደዋለን ፡
ገረመኝ ፡ ደነቀኝ ፡ ብልኋ ፡ የኔ ፡ እመቤት ፡ ነ
ገር ፡ ያውቃሉ ፡
ከእህል ፡ እንኳ ፡ ነጩ ፡ እየተመረጠ ፡ በእሳት
እየሰማ ፡ እየተጋገረ ፡ ይበላ ፡ ስላሉ ።
እኔም ፡ ገረዳቸው ፡ ምን ፡ እቸገራለሁ ፡
ስለነጭ ፡ ቤትነት ፡ ጠንቅቄ ፡ አውቃለሁ ፡
እንጨት ፡ እንደሁ ፡ ሞልቷል ፡ አጋይበታለሁ ።

ገበሬው ፡ ሰማሽ ፡ ወይ ፡ ተዋበች ፡ የትንሣኤው ፡ በዓል
ፍስኩ ፡ ነገ ፡ ነው ፡ ባለፈውም ፡ ጊዜ ፡ ተነጋግረንዋል
አባትና እናትሽጋም ፡ ጠዋት ነው እምንሄደው
እስቲ ፡ የድርጅቱ ፡ ንገሪኝ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሳንጠይቃቸው ፡
ዝም ፡ ብለን ፡ ቀረን ፡ ሄደን ፡ ሳናያቸው ።
አሁን ፡ ደግሞ ፡ ነገ ፡ እንቀራለን ፡ ብትይ ፡
ካገር ፡ እጠፋለሁ ፡ ሁለተኛም ፡ ሄጄ ፡ ዓይናቸ
ውንም ፡ አላይ ።
ስለዚህ ፡ አትጥፋ ፡ ካገር ፡ አትውጣ ፡ ካልሽ ፡
ሁሉም ፡ ተሰናድቶ ፡ ሄደን ፡ እንያቸው ፡ ነገ ፡
ጠዋት ፡ ተነሽ ።
ሰው ፡ መሆናችንን ፡ ዓይናቸውም ፡ ይየን ።
ጸሎታቸው ፡ እኮነው ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ያበቃን ።

የገበሬው ፡ ሚ ፡ ተገ
ኛንና ፡ አፈራሁን ፡
ትጠራና ፡
እናንተ ፡ ሁለታችሁ ፡ የታዘዛችሁት ፡
ዕቃ ፡ አሰናዱ ፡ እኛም ፡ ተነስተናል ፡ እንዳያ
ልፍ ፡ ሰዓት ።

ጆንበር ፡ ሳትጠልቅብን ፡ ቶሎ ፡ እንድንደርስ
እንግዲህ ፡ ተነሱ ፡ በሉ ፡ እንገስግስ ፡፡



አፈ ፡ ገረ ፡ ጠላዋንና ፡ የዶሮ ፡ ዳቦዋን ፡ ይዛ ፡ አ ፡ ተገኘ ፡ ሙክቱን ፡ ስቦ ፡ በ፫ ፡ አህዮች ፡ በያይነቱ ፡ እህል ፡ ጭኖ ፡ ገበሬውና ፡ የገበሬው ፡ ሚ ፡ በአጌጡ ስጋር ፡ በቅሎዎች ፡ ተቀምጠው ፡ ሲሄዱ ፡ በዚህ ፡ ሥዕል ፡ ይታያሉ ፡፡

ከተዋበች ፡ አባት ፡ ቤት፡ልጅ፡ ብቅ ፡ ብ ሎ፡አይቶ፡ተመልሶ፡

አንድ ፡ ወንድና፡አንድ ፡ ሴት ፡ በተሽቆጠቆጡ
ዕቃቸው ፡ ባማረ ፡ በቅሎ ፡ የተቀመጡ ፡፡
አንደኛውም ፡ መሶብ ፡ ሁለተኛው ፡ ገንቦ ፡
ተሸክመዋል ፡
፫ኛው ፡ ደግሞ ፡ ፫ ፡ የተጫኑ ፡ አህዮች፡ ይነዳል
እንዲሁም ጋራ፡የሚያክል፡ሙክት፡ይጐትታል
የነዚህ፡ሰዎች፡ አመጣጥ፡ወደዚህ፡ይመስላል ፡፡
እስቲ ፡ ብቅ ፡ ብዬ ፡ ደግሜ ፡ ልያቸው ፡

ወደኛው ፡ እንዲሆን ፡ ሰዎቹ ፡ መምጫቸው ።
አሁንስ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ አይጠረጠርም ፡
ጉራ ፡ የሚሉበት ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የለም ።
መጡ ፡ ተዳረሱ ፡ ደግሜ ፡ ልናገር ፡
ማዘጋጀት ፡ ያሻል ፡ መቀመጫ ፡ ወንበር ።

ብሎ ፡ መምጣታቸውን ፡ ገብቶ ፡ ሲናገር ።

አባት ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ያያል ፡

ምነው ፡ መሰለችኝ ፡ ያች ፡ ተዋበች ፡ ልጄን
እምላክ ፡ አያልቅበት ፡ ሰጥቷቸው ፡ ይሆን ።
ጠጋ ፡ ጠጋ ፡ ሲሉ ፡ ይኸው ፡ ተዳረሱ ፡
ባኋን ፡ ይመስለኛል ፡ ፩ኛውም ፡ ከነሱ ።
እስቲ ፡ ዝግ ፡ ልበል ፡ ለወሬም ፡ አልቸኩል ፡
እስቲታወቅ ፡ ቁርጡ ፡
ከምነዜውን ፡ አግኝተው ፡ እንዲህ ፡ አምረ
ው ፡ አጌጡ ።
እኔውም ፡ ቂሉ ፡ ነኝ ፡ በጣሙን ፡ ተሞኘሁ ።
ከተለያየንም ፡ ይኸውና ፡ ዓመት ፡ ነው ፡
ሰውም ፡ ከሠራና ፡ እምላክም ፡ ከሰጠው ፡
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይፈጅም ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ ነው ።
እንግዴህ ፡ ይኸውና ፡ ቁርጡን ፡ አውቄአለሁ
እራሳቸው ፡ ናቸው ፡ አረጋግጫለሁ ።

ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ለናትዬዋ ፡ ይንግርና ፡ ሲስንዳዱ ፡
ይደርሳሉ ፤ በዕልልታ ፡ ተቀበለዋቸው ፡ ይሳሳማሉ ።

ገበሬው ፡

አባባና ፡ እማማ ፡ እንደምን ፡ አላችሁ ፡

እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡በጣሙን፡ ደህና፡ነን፡
እኛ ፡ ልጆቻችሁ ።
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ባለመጠየቃችን ፡
ሳይገባን ፡ አልቀረም ፡ ሐዘን ፡ በልባችን ፡
እንግዲህ ፡ ባጭሩ ፡ ሐተታውን ፡ ትተን ፡
ማሩን ፡ ይቅር ፡ በሉን ፡ እንዳትቀየሙን ።
ሳንጠይቃችሁ ፡ ብዙ ፡ ዘግይተናል ፡
መቀየማችሁም ፡ በርግጥ ፡ ይሰማናል ፡
እናት ፡ ይቅርታ ፡ ልመና ፡ ፊታችሁ ፡ ወድቀናል ።
ተነሱ ፡ አትውደቁ ፡ ጠላታችሁ ፡ ይውደቅ ፡
በጣም ፡ ናፍቀናችኋል ፡ እንጫወት ፡ ይልቅ።
ከነመኖራችሁ ፡ መች ፡ ሰምተን ፡ እናውቃለን፡
ግራ ፡ እየገባን ፡ ስንዋልለው ፡ አለን ፡
የክርስቶስን ፡ ጥበብ ፡ ማን ፡ ያውቃል ፡
ምሥጢሩን ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ አኑሮ ፡ ይኸው ፡ አገናኘን ፡
እዚህ ፡ ተደፍታችሁ ፡ ይቅርታ ፡ የምትሉን ፡
ወይ፡ እናንተ፡ ወይ፡ እኛ፡ብንሞት፡ አንደኛችን፡
ቀረን ፡ ሳንገናኝ ፡ እንደተለያየን ።
እኔም ፡ እናታችሁ ፡ እሱም ፡ አባታችሁ ፡
ይቅር ፡ ብለናችኋል ፡ እናንተ ፡ ሁለቱ ፡ ባል
ና ፡ ሚስቶቹ ፡ አሁን ፡ እንዳላችሁ ፡
አምላክ ፡ ዘለዓለም ፡ ባልንጀራ ፡ ያርጋችሁ ፡
ረድኤታችንም ፡ ፍጹም ፡ አይለያችሁ ።



ብለው ፡ መርቀው ፡ የመጣውን ፡ ሙክት ፡ አርደው ፡ ጕረቤት ፡ ሁሉ ፡ ተጠርቶ
በደስታና፡ በጨዋታ ፡ ከተጋበዙ ፡ በኋላ ፡ ሲመክሯቸው ፡ በሥዕል ፡ ይታያል ።

አባት ፡ እንግዲህ ፡ ልጆቼ ፡ ስሙኝ ፡ ልምከራችሁ ፡
አባትና ፡ እናት ፡ ለልጁ ፡ የሚመክረው ፡
የማይጠቅመውን፡ ሳይሆን፡ የሚጠቅመውን
ነው ።
እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ማግኘትና ፡ ማጣት ፡
እኛም ፡ ሳንነግራችሁ፡ እናንተም ፡ አያችሁት ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ ኃላፊ ፡ ነው፡
ግንድም ፡ ሆነ ፡ ብረት ፡ ሁሉ ፡ ወዳቂ ፡ ነው ።
እናንተ ፡ ልጆቼ ፡ ከተጋባችሁበት ፡ ዕለት ፡
ጀምራችሁ ፡

ከመልከስከስ ፡ ጠባይ ፡ በጣም ፡ ንጹሕ ፡ ናቸሁ ፡
እወቁት ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ አምላክ ፡ የረዳችሁ ፡
አሁን ፡ በበኩሌ ፡ እኔ ፡ የማስረዳችሁ ፡
በንጽሕናችሁ ፡ እንዲሁ ፡ እንዳላችሁ ፡
የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ እንዳደረባችሁ ፡
እንድትኖሩልኝ ፡ ነው ፡ በሕግ ፡ ጸንታችሁ ፡
በተክሊል ፡ ቆርባችሁ ።
ፈቃዴ ፡ ነውና ፡ እንዲህ ፡ እንድትሆኑልኝ ፡
ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ እሺ ፡ እንደምትሉኝ ።

የገበሬው ፡ ሚ ፡ አባባ ፡ የኔ ፡ አባት ፡ ስማኝ ፡ ልንገርህ ፡
የኔን ፡ የልጅህን ፡ ልቤን ፡ ታውቀዋለህ ፡
በጣም ፡ ተደሰትኩኝ ፡ በዛሬው ፡ ምክርህ ።
እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ስትመክረኝ ፡ ቀርቶ ፡ የነፍሴን ፡
መዳኛ ፡ የምወጣበትን ፡
ካልከኝ ፡ እምቢ ፡ አልልም ፡ የምሞትበትን ።
እሱም ፡ ቢሆን ፡ ባሌ ፡ በጠባይም ፡ በግብር ፡
በጣም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ፡
አምላኩንም ፡ ፈሪ ፡ ሰውንም ፡ አክባሪ ፡ ነው ፡
አሁን ፡ እንዳልከውም ፡ በመልከስከስ ፡ በኩል ፡
(ጠባይ) ፡ አይጠረጠርም ፡ ፍጹም ፡ ንጹሕ ፡
ሰው ፡ ነው ።
እኔን ፡ እንደጠየቅህ ፡ እሱንም ፡ በተራው ፡
እንዲሁ ፡ ጠይቀህ ፡
የሚሆን ፡ ከሆን ፡ ይሆናልም ፡ ካለህ ፡
በሚመስልህ ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ ትችላለህ ፡
እኔ ፡ ግን ፡ እርግጡን ፡ ደግሜ ፡ ልንገርህ ።
ከዚህ ፡ ከማፈቅረው ፡ ከእኩያ ፡ ባሌ ፡ ከተለያየሁኝ
እንኳን ፡ ዓለምና ፡ መኖርም ፡ አልመኝ ፡

**አባት ፡ የልጁን ፡ ባል ፡ በተራው ፡ ሲጠይቅ ፡**

እሁን ፡ ካንተ ፡ በፊት ፡ ከልጄ ፡ ጋር ፡ ነበርን
ስለዚህ ፡ ዓለም፡ጉዳይ፡በሰፊው ፡ ተወያየን ።
በተክሊል፡ቆርባችሁ፡አብራ ችሁ፡እንድትኖሩ
ብዬ ፡ ብጠይቃት ፡
በጣም ፡ ተደሰተች ፡ በፍጹም ፡ ሳይከፋት ።
እሷን ፡ እንደጠየቅሁ ፡ አንተንም ፡ በተራህ ፡
መጠየቅ ፡ ስላሻኝ
ይኸን ፡ ላማክርህ ፡ ጠርቼህ ፡ አለሁኝ ፡
መሆን፡ አለመሆኑን፡ መልሱን፡ እንድትነግረኝ።

**ገበሬው ፡**

የአበባዬ ፡ የሚስቴ ፡ አንቱ ፡ የኔ ፡ አባት ፡
እኔም፡በበኩሌ፡ያድምጡኝ፡ልንገርዎት ፡
እንኳንስ ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ በሕይወቴ፡ ባለሁበት፡
እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለይ፡
በእቶ ፡ ሞት ፡ ዳኝነት ፡
አልጠራጠርም ፡ ሚስቴ ፡ ከፊኔ ፡ ናት ።
ተክሊል ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ እስከ፡ መጨረሻው፡
ጠንቅቄ ፡ አውቃለሁ ፡
ከእንግዲህስ ፡ ወዲያ ፡ እኔስ ፡ ከሷ ፡ ሌላ ፡ ማን፡
ፍለጋ ፡ እሄዳለሁ ።
ክብሩ ፡ ይስፋ ፡ ፈጣሪ ፡ ኃብትም ፡ ሆነ ፡ ጸጋ ፡
ልጅም ፡ አግኝተናል ፡
ከመቀጠር ፡ ወጥተን ፡ መቅጠርም ፡ ችለናል ፡
ከብድርም ፡ ወጥተን ፡ ለማበደር ፡ በቅተናል ።
ሕጉንስ ፡ ብንፈጽም ፡ ለምን ፡ ቅር ፡ ይለኛል ።
እንግዲህ ፡ ይኸን፡ ቃሌን ፡ በውነት፡ ይመኑና ፡
ባሰቡት ፡ ይፈጽሙ ፡ ቶሎ ፡ ይበሉና ።

**አባት ፡**

እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔር ፡ መን
ፈሱን ፡ ያሳደረባቸው ፡

መልክ ን፡ ከጠባይ ፡ ጋር ፡ አዋህዶ፡የሰጣቸው፡
የግብራቸው ፡ ማማር ፡ የትሕትናቸው ፡
ናዝራዊው፡ ኢየሱስ ፡ ሁል፡ ጊዜ፡አይለያቸው፡
አሁንም ፡ ላይ ፡ በላይ ፡ በረከት፡ ይስጣቸው ።
አሁን ፡ ተነሥቼ ፡ ወደአለንቆ ፡ ማርያም ፡
ሁለቱንም ፡ ወስጄ ፡
መመለስ ፡ ያሻኛል ፡ በሥጋው ፡ በደሙ ፡ በተ
ክሊል ፡ አጽንቼ ።



ይሉና ፡ ከተባለው ፡ ቤት ፡ ከ ፡ ገበሬውና ፡ የገበሬው ፡ ሚ፡ ጋብቻቸውን ፡ በመ
ምሕር፡ ዘለቀ ፡ ወ፡ ሰ፡ አማካይነት ፡ በተክሊል ፡ ሲያጸኑ ፡ በሥዕል ፡ ይታያሉ ።

እናት ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ከመጀመሪያውም ፡ በሕግ ፡
ሲጋቡ ፡
ለሥራቸው ፡ እንጂ ፡ ሁሌ ፡ የሚተጉት ፡
ይኸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ያመንዝራን ፡ ጠባይ ፡
በፍጹም ፡ ሳያውቁት ፡
የሕጉን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተክሊል ፡ ፈጸሙ
በአምላክ ፡ ቸርነት ።
እንግዲህ ፡ ተመስገን ፡ ዳግመኛ ፡ ፈጠርከኝ ፡
የልጄን ፡ በሕግ ፡ መጽናት ፡ ባይኔ ፡ ካሳየኸኝ
ተመስገን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ወሮታ ፡ አለህ
ዕድሜ ፡ እየሰጠህ ፡ ይኸን ፡ ታሳያለህ።

የገበሬው ፡ ሚ እንግዲህ ፡ አሳብ ፡ ለሃሣብ ፡ ከተፈጻጻምን ፡
ቤታችን ፡ ባዶ ፡ ነው ፡ እንሂድ ፡ ፍቀዱልን ፡
ለወደፊቱ ፡ ግን ፡ እግዜር ፡ ደህና ፡ አድርጎ
ጤንነት ፡ ከሰጠን ፡
እናያችኋለን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እየመጣን ፡
እኛም ፡ እስክንመጣ ፡ እንዳይቸግራችሁ ፡
ለልብሳችሁ ፡ ይሁን ፡ ሃምሣ ፡ ብር ፡ እንካችሁ ፡
ምንም ፡ ችግር ፡ የለም ፡ ሳለን ፡ ልጆቻችሁ ፡
በሉ ፡ ደህና ፡ ሁኑ ፡ አትባቡ ፡ አይዟችሁ ።

ብለው ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ይመለሳሉ ፡

ገበሬው ፡ ይኸው ፡ ቤታችንም ፡ በሙሉ ፡ ሰላም ፡ ነው ፡
ዕቃችንም ፡ ሁሉ ፡ እንደነበረ ፡ ነው ፡
አንድም ፡ አልጠፋብንም ፡ እንዳስቀመጥነው ፡
ነው ፡

የግንቦትንም ፡ ወር ፡ በደስታ ፡ ፈጸምነው ፡
በብዙ ፡ ሰው ፡ ፊትም ፡ ሰው ፡ ለመሆን ፡ የቻልነው
በመተባበርና ፡ ጠንክሮ ፡ በማረስ ፡ ነው ።
ያንን ፡ ሁሉ ፡ ችግር ፡ በመጠንከርና ፡ በሥራ
አስወግደን ፣
ይኸውና ፡ ዛሬ ፡ ባለሐብት ፡ ጌታ ፡ ሆን ፤
የታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ክብሩ ፡ ይስፋ ፡ ተመስገን ።

በተስፋ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

በተስፋ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።